## *መደብ*

ስለ ስሞች ስንወያይ እንዳወሳነው፣ መደብ ሰዎች በሚነጋገሩበት ወቅት ከሚኖራቸው ሚና ጋር የተገናዘበ ሰማዊ ባህሪ ነው፡፡ በንግግር ወቅት፣ የተነጋጋሪዎች ሚና፣ ተናጋሪነት፣ ተነጋሪነት ወይም አድማጭነትና አንዳንድ ጊዜም ታዛቢነት ነው፡፡ ታዛቢ ባለበት እንነጋገር የሚባለውም ለዚሁ ነው፡፡ ተናጋሪ የንግግሩ ምንጭ ስለሆነ፣ አንደኛ መደብ ይባላል፡፡ የሚናገረውም <u>እኔ</u> እያለ ነው፡፡ ተነጋሪው ነገሩ የሚነገረው ሰው ነው፡፡ ስለዚህም ሁለተኛ መደብ ይባላል፡፡ "አንተ ስማ!" እየተባለ ይነገረዋል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ውጭ የሆነ በው ካለ፣ ያ ሰው ሶስተኛ መደብ ይባላል፡፡ <u>እሱ</u> ወይም <u>ይኸ</u> ፣ ወዘተ፣ እየተባለ ይጠቆማል፡፡ እነዚህ ሶስት መደቦች በሁለት አይነት ቅርፅ ይከሰታሉ፡፡ አንደኛው በነፃ ምዕላድ መልክ ሲሆን፣ ሌላኛው በጥገኛ ምዕላድ ቅርፅ ነው፡፡ በመጀመሪያው ቅርፃቸው ሲከሰቱ፣ መደበኛ ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡ እንደ ስሞች ሁሉ ለቁጥርና ለፆታ የተሰያዩ ምዕላዶችን ሊያስከትሉ ወይም ሊያስቀድሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

| መደብ | ነጠላ | ብዙ | አክብሮት |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | አን-ኤ | እነ-አን-ኤ [ እኛ] | |
| 2ኛ ተ | አን-ተ | እነ-አንተ | አንት-ኡ |
| አ | አን-ት-ኢ [ሳንቺ] | | |
| 3ኛ ተ | እርሰ-ኡ | እነ-እርሰ-ኡ | እርሰ-እ [እርስ] |
| እ | እርሰ--ኡ-አ [እርስዋ] | | |
| | | | |

1 የተውላጠ ስም ሰንጠረዥ

ባለፈው ንዑስ ክፍል ስለ ስሞችና ቅፅሎች የርባታ ስርዓት ስንወያይ እንደገለፅነው፣ /-ኢ/ እና /-አ/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ የእንስታይ ፆታ ምዕላዶች ናቸው፡፡ /-ኢ/ የአነደኛ መደብ፣ /-ተ/ የሁለተኛ መደብ ፣ /-ኡ/ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ናቸው፡፡ /እንንኧ-/ አጉዋዳኝ የጥቂት ቁጥር ምዕላድ ነው፡፡ የአክብሮት ምዕላዶቹም ለሁለተኛ መደብ /-ኡ/፣ ለሶተኛ

---

/ፍኧ<u>ልልአ</u>ግኢ/ /ብአርእክኢ/

በግልፅ እንደሚታየው፣ /ል/ በሁሉም ቅርፆች ሊጠብቅ፣ /ር/ ግን በሁለቱ ብቻ ነው የጠበቀው፡፡ ይህ ሁኔታ እንደ <u>ባረከ</u> ያሉ ግሶች የ(ሀ) ክፍል ግሶች አካል ናቸው፣ የሚያሰኝ ነው፡፡

መደብ /-ኦ/ ናቸው፡፡ /-ኤ/ የአንደኛ መደብ ምዕላድ ለመሆኑ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቤት-ኤ 2
ቤት-ህ
ቤት-ኡ

ሶስቱ መደቦች የተለያየ ቅጣይ ምዕላድ እንዳላቸው ግልፅ ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ <u>እንትን</u> እና <u>እንትና</u> የሚባሉ ተውላጠ ስሞችም አሉ፡፡ የመጀመሪያው አንድን ነገር በስሙ ለመጥራት ሳንፈልግ ስንቀር፣ ወይም ስሙ ሲረሳን በምትክነት የምንጠቀምበት ተውላጠ ስም ነው፡፡ ለነገር እንጅ፣ ለሰው አይሆንም፡፡ ለሰው ስም ምትክ የሚሆነው <u>እንትና</u> የሚለው ነው፡፡ አንድን ሰው <u>እንትና</u>! ወይም በቁልምጫ <u>እንትናዬ</u>! ብሎ ለመጥራት ያገለግላል፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያውን ብቻ ተውላጠ-ነገር ልንለው እንችላለን፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

ከእንትናችን ውስጥ እንትን ገብቶበት 3
እንትን አምጥልኝ እንትን እልበት
አንችም ነይልኝ እንትን ትይልኝ

ባገር ቤት እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ አባባል ነው፡፡ አንድ ጭሰኛ ገበሬ ባቄላው ውስጥ ወጥመድ አጥምዶ ያድራል፡፡ ጥዋት ሲሄድ ሚድያቋዋ ይዞ ያገኘዋል፡፡ ባለቤቱን ጠርቶ ቢላዋ ይዛ እንድትመጣና እንድትረዳው ይፈልጋል፡፡ በግልፅ እንዳይነግራት ባለመሬቱ፣ ማለትም ጌታው፣ በአንግድነት መጥቶ ቤቱ ውስጥ ስለሚገኝ፣ ጉዳዩን ሲሰማበት ሆነ፡፡ ከሰማ ደግሞ ይወስድባቸዋል፤ ወጥመዱ የተጠመደበት መሬት የእሱ ነውና፡፡ ስለዚህም ገበሬው ባለቤቱን ይጠራትና፣ ከእንትናችን ውስጥ ...፣ አላት ይባላል፡፡ ሞኝ ጌታ ካልሆነ በስተቀር፣ ይችን እንኳዋ መረዳት አያቅተውም! ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው መደቦች ከላይ እንደሚታዩት ባሉ መደበኛ ተውላጠ ስሞች ብቻ ሳይሆን፣ በጥገኛ ምዕላድነትም ይከሰታሉ፡፡ በዚህ መልክ የሚከሰቱት አፀፋ ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡ አፀፋ የሚያሰኛቸው የመደበኛዎቹ እጣፊ ወይም አምሳል መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህም የሚከሰቱት በስሞችና በግሶች ላይ ነው፡፡ በግሶች ላይ የሚከሰቱት በሁለት መልክ ነው፡፡ በቀዳማይ አንቀፅና ቦዝ አንቀፅ በሚባሉት አምዱን ተከትለው፣ በካልዓይ አንቀፅ ደግሞ አምዱን ቀድመው ይገባሉ፡፡ ስለ አንቀፅ ወደ ሁዋላ እንወያያለን፡፡ አሁን ሁኔታውን <u>ሰበሬ</u>

ርባታ

በሚለው ግስ እምድና <u>ሰብራት</u> በሚለው ስም አማካኝነት ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

| መደብ | ካልዓይ | ቀዳማይ | | ስም | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | እ-ሰብር | ሰበር-ኩ[7] | | ሰብራት-የ | |
| 2ኛ ተ | ት-ሰብር | ሰበር-ሀ | | ሰብራት-ሀ | |
| እ | ት-ሰብር-ኢ | ሰበር-ሽ | < /ሰበር-ሀ-ኢ/ | ሰብራት-ሽ | < /ሰብራት-ሀ-ኢ/ |
| 3ኛ ተ | ይ-ሰብር | ሰበር-ኸ | | ሰብራት-ኡ | |
| እ | ት-ሰብር | ሰበር-ኸች | </ሰበር-ኸት-ኢ/ | ሰብራት-ዋ | < /ሰብራት- ኡ-እ/ |
| ብ | እ-ን-ሰብር | ሰበር-ን | | ሰብራት-አች[8]-ን | |
| | ት-ሰብር-ኡ | ሰበር-አችሁ | | ሰብራት-አች-ሁ | </ሰብራት-አች-ሀ-ኡ/ |
| | ይ-ሰብር-ኡ | ሰበር-ኡ | | ሰብራት-አቾ-ው | /ሰብራት-አች-ኸ-ኡ/ |

4 የመደብ፣ የቁጥርና የፆታ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ በካልዓይ አንቀፅ /ኧ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የአንደኛ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች ናቸው፡፡ /-ኢ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ስትሆን፣ አገባብዋም አምዱን ተከትላ ነው፡፡ /-ን/ የአንደኛ መደብ፣ /-ኡ/ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላዶች ናቸው፡፡ መደብ፣ ቁጥርና ፆታ በተለያዩ ምዕላዶች እንደተገለፁ መረዳት ይቻላል፡፡ በቀዳማይ አንቀፅ ደግሞ እነዚሁ የመደብ ምዕላዶች /-ኩ/፣ /-ሀ/ እና /-ኸ/ በሚሉ ቅርፆች በአምዱ መድረሻ ላይ ይታያሉ፡፡ የፆታና የቁጥር ምዕላዶቹ በተናጠል ሳይሆን ከመደብ አመልካቾቹ ጋር እየተዋሀዱ ገብተዋል፡፡ በስሙ ላይ ደግሞ የመደብ ምዕላዶቹ /-የ/፣ /-ሀ/ እና /-ኡ/ ሆነው ይታያሉ፡፡

በግሶቹ ላይ የሚታዩት የመደብ፣ የቁጥርና የፆታ ምዕላዶች በአንድነት የባለቤት አፀፋ ይባላሉ፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት የሆነን ስም የሚያመለክቱ ወይም የሚተኩ ምዕላዶች ናቸው፡፡ እነሱ በግሱ ላይ ስለሚታዩ፣ ስሙ በግሀድ ላይከሰት ይችላል፡፡

አንድ ስም የአረፍተ ነገር ባለቤት መሆኑ የሚታወቀው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚገኝበት ቦታ ሲሆን፣ ሁለተኛው በግሱ ላይ በሚታየው የአፀፋ ምዕላድ አማካኝነት ነው፡፡ በስሙ ላይ የሚታዩት አፀፋዎች የሚያመለክቱት፣ ስሙ የሚጠቁመው ነገር የማን መሆኑን ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት አገናዛቢ አፀፋ እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡

---

[7] በቀዳማይ አንቀፅ የአንደኛ መደብ ምዕላድ ቅርፅ /-ሁ/፣ የሁለተኛ መደብ ደግሞ /-ህ/ ሆኖ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው አምዱ በአናባቢ የሚጨርስ ሲሆን ነው፡፡

[8] /-አችች-/ በአገናዛቢ ሰሞች ላይ የሚገኘው የብዙ ቁጥር ምዕላድ ነው፡፡ በግሶች ላይ የሚገኝበት ምክንያት፣ የቀዳማይ አንቀፅ ግሶች ከስም የመጡ ስለሆነና፣ የስሙ የብዙ ቁጥር ምዕላድም አብሮ በመምጣቱ ነው፣ የሚል ነው፡፡ ዝርዝሩን ከሀድሰን (1981) ይመልከቱ፡፡

ርባታ

ከላይ እንደሚታየው፣ መደቦች ነጠላ ወይም ብዙ ተብለው በቁጥር፣ እንዲሁም ተባዕታይ ወይም አንስታይ ተብለው በፆታ ይለያሉ፡፡ ይህን ቀደም ሲል በስሞች ርባታ ላይም አይተነዋል፡፡ አሁንም በግሶች ላይ እያየነው ነው፡፡ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ የአነስታይ ፆታ ምዕላድዋ /-ኢ/ ስትሆን፣ የሶስተኛ መደብ የአንስታይ ምዕላድ ደግሞ /-ት/ ነች፡፡ እሰዋም የምትገኘው በካልዓይ አንቀፅ አምድ መነሻ ላይ እና በቀዳማይ አንቀፅ አመድ መድረሻ ላይ ነው፡፡ በዚህ አምድ ከፆታ ምዕላድዋ ከ/-ኢ/ ቀድማ ትገኛለች፡፡ ሁለት የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች አሉ ማለት ነው፡፡ አንደኛው /ይ-/ን እና /-ሽ-/ን ይዞአል፡፡ የመጀመሪያው በካልዓይ፣ ሁለተኛው በቀዳማይ አንቀፅ ይገኛል፡፡ ሁለተኛው /-ት-/ን ብቻ ይዞአል፡፡ እሰዋም በሁሉቱም አንቀፆች ትገባለች፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

| <u>ካልዓይ</u> | <u>ቀዳማይ</u> | |
|---|---|---|
| /ይ-ስሽብር-/ | /ሰሽብብሽር-ሽ/ | 5 |
| /ት-ስሽብር-/ | /ሰሽብብሽር-ሽ[9]-ት-ኢ/ | ሰበረች |

በቀዳማይ አንቀፅ፣ የግሱን አምድ ተከትላ ለትመጣ፣ /-ት-/ በ/-ኢ/ ምክንያት ወደ ላንቃዊነት ትለወጥና [ች] ትሆናለች::

እነዚህ ባለፈው ክፍል ለለ ስሞች ርባታ ለንወያይ ያየናቸው የፆታ ምዕላዶች ናቸው፡፡ በዚያ ላይ፣ ማንኛውም ስም ተባዕታይ ወይም አንስታይ እንደሆነ ገልፀን፣ የወልና የግዑዝ ፆታ የሚባሉ ክፍሎች እንደሌሉ ጠቁመን ነበር፡፡ በዚህ በግሱ ርባታ ውስጥ የምናየው ሁኔታም ይህን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በግሱ ውስጥ የምትገኘው የአንስታይ ፆታ ምዕላድ /-ኢ/ ብቻ ነች[10]፡፡ የወልና የግዑዝ የሚባሉ የፆታ ክፍሎች ቢኖሩ ኖሮ፣ እንደ አንስታይ ፆታዋ ምዕላድ በተለያየ ቅርፅ በግሱ ርባታ ላይም መታየት ነበረባቸው፡፡

መደብ አመልካች ምዕላዶች ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የሚታዩት ብቻ አይደሉም፡፡ እነዚህ ባለቤት ወይም ባለገንዘብ የሆነን ስም መደብ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሌላ ተሳቢ የሆነን ስም መደብ የሚያመለክቱ ምዕላዶችም አሉ፡፡ እነዚህ ግን በሁሉም ግሶች ላይ ሳይሆን፣ ሳቢ በሚባሉት ላይ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሳቢ ግሶች የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር የሚቀናጁ ናቸው፡፡ አቀነጃጀቱን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን፡፡ የአፀፋዎቹን አይነት ግን አሁንም <u>ሰበረ</u> በሚለው ሳቢ ግስ አማካኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

---

[9] ይህ አናባቢ /-ሽ-/ በስነ-ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ምክንያት የገባ አናባቢ ድምፅ ነው፡፡
[10] ይህን የምንለው የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችውን /-አ/ ሳንዘነጋ ነው፡፡

ርባታ

| መደብ | ነጠላ | | ብዙ | |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | ሰበር-ኧ-ኝ | | ሰበር-ኧ-ን | |
| 2ኛ ተ | ሰበር-ኧ-ህ | | ሰበር-ኧ-አችሁ | </ሰበር-ኧ-አችች-ሁ-ኡ/ |
| አ | ሰበር-ኧ-ሽ | </ሰበር-ኧ-ሁ-ኢ/ | | |
| 3ኛ ተ | ሰበር-ኧ-ው | | ሰበር-ኧ-አቸሁ | </ሰበር-ኧ-አችች-ኡ/ |
| አ | ሰበር-ኧ-አት | | | |

6. የተሳቢ ምዕላድ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚታየው ምዕላድ /-ኧ/ ሲሆን፣ እሱም ከፍ ሲል ያየነው የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው፡፡ ከእሱ ቀጥሎ የሚገኙት የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው፡፡ ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና ከሶስተኛ መደብ በስተቀር፣ የሌሎቹ አፀፋዎች ቅርፅ ከባለቤት አፀፋ ምዕላዶች ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የአንደኛ መደብ የባለቤት አፀፋ የብዙ ቁጥር /-ን/ ሲሆን፣ የተሳቢውም እንደዚሁ /-ን/ ነው፡፡

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የምዕላዶቹን ቅደም-ተከተላዊ አገባብ የሚመለከት ነው፡፡ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው ሁል ጊዜም የባለቤት አፀፋ ሲሆን፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚመጣው የተሳቢው አፀፋ ነው፡፡ የባለቤቱም ሆነ የተሳቢው አፀፋ የመደብና የቁጥር ወይም የፆታ ምዕላድ ውሁድ ነው፡፡ ምዕላዶቹ ከመዋሀዳቸው በፊት የሚገኙበት ቅደም-ተከተላዊ ስርዓትም መደብ አመልካቹ ቀድሞ፣ ቁጥር ወይም ፆታ አመልካቹ እሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ /-ሽ/ የሚለው የሁለተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ፣ የመደብ አመልካቹ /-ሀ/ እና የአንስታይ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ ውሁድ እንደሆነ፣ ከፍ ሲል ተገልፆአል፡፡ የእነዚህ ምዕላዶች ቅደም-ተከተላዊ አቀማመጥም /-ሀ-ኢ/ ሲሆን፣ ወደ [-ሽ] የሚለወጡት በለነ-ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ነው፡፡ ሂደቱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ወቅታዊነትም አለው፡፡ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ በየግሱ የትዕዛዝ እንቀፅ አምድ መድረሻ ላይ ብቻዋን ትገኛለች፡፡ ይሀም ሰበሪ (/ስ - ብኧር-ኢ/ ) ስንል ነው፡፡

እስካሁን ያየናቸው ስማዊ የተሳቢ አፀፋዎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ የሚያመለክቱት ተሳቢ የሆነ ስማዊ ሀረግን ነው፡፡ ከነዚህ ሌላ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች የሚባሉ አሉ፡፡ እነዚህ የሚያመለክቱት የተለያየ ተውሳከ ግሳዊ ተግባር ያላቸውን መስተዋድዳዊ ሀረጎች ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ [በአዲሱ ብዕር] ደብዳቤ ፃፍ-ኧ-በት 7

(ለ) ካሳ [ገነትን] ገንዘብ ወሰድ-ኧ-ባት </ብ-አት/

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው /ኧ/፣ የባለቤቱ አፀፋ ነው፡፡ ከእሱ ቀጥሎ የሚገኘው /-በት/ የሚለው የመስተዋድድ ሀረግ አፀፋ

ነው፡፡ ይህም ከ/ብ/ እና ከ/-ት/ የተጣመረ ድርብ ምዕላድ ነው፡፡ እፀፋነቱም [በአዲሱ ብዕር] ሰሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ ሀረጉ [በ] የሚለው መሰተዋድድና [አዲሱ ብዕር] የሚለው ሰማዊ ሀረግ ቅንጅት ነው፡፡ የስማዊ ሀረጉ አፀፋ /-ት/ ነች፡፡ እሰዋም ከመሰተዋድዱ ከ[በ] ጋር ተቀናጅታ /-በት/ ሆናለች፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ፣ [ገነትን] የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ መሰተዋድዱ [ን][11] ሲሆን፣ ከእሱ ጋር የተዋቀረው ደግሞ ገነት የሚለው ሰም ነው፡፡ በግሱ ላይ ይህን ሀረግ የሚያመለክተው አፀፋ /-ባት/ ነው፡፡ እሱም የ[በ] እና ገነት የሚለው ሰም አፀፋ የሆነችው የ/-አት/ ቅንጅት ነው፡፡ ይህች ምዕላድ ከፍ ሲል ባየነው የግሰ ዝርዝር ርባታ ውሰጥም በተሳቢ አፀፋነት ትታያለች፡፡

መሰተዋድዳዊ አፀፋዎች በግሶች ለሚገለፁ ተግባራት ተጎጅ ወይም ተጠቃሚ መሆንን ሊያመለከቱ ይችላሉ፡፡ ተጎጅነት [በ] በሚለው፣ ተጠቃሚነት ደግሞ [ለ] በሚለው መሰተዋድድ አማካኝነት ይገለፃል፡፡ ሰለሁኔታው የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ እናቱ መጡ-በት 8
(ለ) ካሳ እናቱ መጡ-ለት

በመጀመሪያው ምሳሌ /-በት/ የሚለው መስተዋድዳዊ አፀፋ በእናቱ መምጣት ካሳ ተጎጅ መሆኑን ይገልፃል፡፡ መመጣታቸው እሱን ችግር ላይ የሚጥል ሊሆን ይችላል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ፣ የተገለፀው የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ካሳ በእናቱ መምጣት ተጠቃሚ ነው፡፡ ይህን ለማመልከት /-ለት/ የሚለው አፀፋ በግሱ ላይ ይታያል፡፡ በዚሁ መሰረት [በ]ን እና [ለ]ን የተጎጅና የተጠቃሚ መሰተዋድድ አፀፋ ልንላቸው እንችላለን፡፡

ከፍ ሲል እንደጠቆምነው፣ የተሳቢ አፀፋዎች የሚገኙት በሳቢ ግሶች ላይ ነው፡፡ የመሰተዋድድ አፀፋዎች ግን ነው ከሚለው የመሆን ግሰ በስተቀር በሌላ በማንኛውም ግስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጅ ከሳቢ ግሰ ላይ በሚገኙበት ጊዜ፣ የተሳቢው አፀፋ በቦታው ሊገኝ አይችልም፡፡ ግሱ የተሳቢ አፀፋን በሚያሳይበት ጊዜ ደግሞ የመስተዋድድ አፀፋው በቦታው አይታይም፡፡ ሰለዚህም፣

*ካሳ መፅሀፉን ለእኔ ሸፈን-ኸ-ው-ልኝ 9

ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ግሱ /-ው/ የሚለውን የተሳቢ አፀፋና /-ልኝ/ የሚለውን የመሰተዋድድ አፀፋ በማሳየቱ ነው፡፡ ማሳየት የሚችለው ከሁለቱ አንዱን ብቻ ነው፡፡ ይህም ግሱ ከባለቤቱ አፀፋ ሌላ፣ አንድ ተጨማሪ

[11] /-ን/ እንደ ተሳቢ አመልካች ብቻ ሳትሆን፣ እንደ መስተዋድድም ታገለግላለች፡፡ ለምሳሌ፣ *ወደ አገሩ ሂደ*፤ በማለት ፋንታ *አገሩን ሂደ*፤ እንላለን፡፡ አገሩን ከሚለው ላይ የምትታየው /-ን/ ወደ በሚለው መስተዋድድ ፋንታ የገባች ነች፡፡ መኪናውን አፈር ጫነበት፤ ስንልም *በመኪናው* አፈር ጫነበት፣ ማለታችን ስለሆነ፣ *መኪናውን* በሚለው ስም ላይ የምትታየው /-ን/ በመኪናው በሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ መነሻ ላይ የምትገኘው የ/በ/ ምትክ ነች፡፡ በዚህ አይነት /ን/ የተለያዩ መስተዋድዶችን ስለምትተካ፣ ተውላጠ-መስተዋድድ ልትባል ትችላለች፡፡

አፀፋ ብቻ የመያዝ ችሎታ እንዳለው ያሳያል። የባለቤቱ አፀፋ ምን ጊዜም አይቀሬ ነው። የተሳቢ አፀፋዎች ግን ሲቀሩ ይችላሉ። በጥቅሉ የአማርኛ ግስ ቅርፅ የሚከተለው ይመሳሳል ብሎ መቁዋጨት ይቻላል።

(ሀ) አምድ-የባለቤት-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ 10
ምሳሌ፣ ሰበር-ኸ-ሽ < /ሀ-ኢ/
ሰበር-ኸ-ብኝ

(ለ) የባለቤት አፀፋ-አምድ-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ
ምሳሌ፣ ይ-ሰብር-ሽ- </ሀ-ኢ/
ይ-ሰብር-ብኝ-

የመጀመሪያው የቀዳማይ፣ ሁለተኛው የካልዓይ አንቀፅን የግስ ስርዓት ይከተላል። በሁለቱም አንቀፆች መደብና ፆታ ወይም መደብና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች አንድም ተለያይተው አለያም ተዋህደው ሊከሰቱ ይችላሉ። ተዋህደው የሚከሰቱት አምዱን ተከትለው ሲመጡ ነው። ይህም በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፅ ነው። ስለ አንቀፅ ከዚህ ቀጥለን እንወያያለን።

## አንቀፅ

አንቀፅ በአንድ ግስ የሚገለፅ ድርጊት ወይም <u>ሁነት</u> መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ በመጨረሻም ተፈፅሞ ያለቀ ወይም ያላለቀ መሆኑን የሚያሳይ ለዋሰዋዊ ባህሪ ነው። የተፈፀመ ድርጊትን የሚገልፅ ግስ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ፣ ያላለቀ ድርጊትን የሚገልፅ የካልዓይ አንቀፅ ግስ ይባላል። የሁለቱ አንቀፆች ቅርፅም የተለያየ ነው። ልዩነቱን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት።

| <u>ቀዳማይ</u> | | <u>ካልዓይ</u> | | |
|---|---|---|---|---|
| /ሰኸብብኸር-/ | ሰበር- | /-ሰኸብር-/ | -ሰብር- | 1 |
| /ግኸድድኸል-/ | ገደል- | /-ግኸድል-/ | -ገድል- | |
| /ፍኸልልኸግ-/ | ፈለግ- | /-ፍኸልልግ-/ | -ፈልግ- | |
| /ዝኸምምኸር-/ | ዘመር- | /-ዝኸምምር-/ | -ዘምር- | |

እነዚህ የመደብ፣ የቁጥር ወይም የፆታ ምዕላድ የቀራቸው አይነተኛ የአንቀፅ አምዶች ናቸው። ቅርፃቸውም እንደሚከተሰው ነው።

ቀዳማይ : / ተ$_1$ኸተ$_2$ተ$_2$ኸተ$_3$-/ 2
ካልዓይ : /-ተ$_1$ኸተ$_2$(ተ$_2$)ኸተ$_3$ -/

የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ያጠብቃል። ከመነሻው ተናባቢ በሁዋላና ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /ኸ/ የሚለውን አናባቢ ያስገባል። የካልዓይ አንቀፅ አምድ ደግሞ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ ብቻ ይህንኑ አናባቢ

ያስገባል፡፡ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ሊያጠብቅ ወይም ላያጠብቅ ይችላል፡፡ ተናባቢው (ተ2) በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠውም ይህንኑ ሁኔታ ለማሳየት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት አንቀፆች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከእነሱ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተለያዩ የድርጊትና የሁነት አይነቶችን የሚገልፁ አንቀፆች መፍጥር ይቻላል፡፡ ከነዚህ መካከል አራቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) አቃጅ አንቀፅ 3
(ለ) ወጣኝ አንቀፅ
(ሐ) ቀጣይ አንቀፅ
(ሰ) ጨራሽ አንቀፅ

## አቃጅ አንቀፅ

አቃጅ አንቀፅ የሚባለው አንድ ድርጊት ይፈፀም ዘንድ መታቀዱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ልዩ ምለከቱ /ል-/ የሚል ምዕላድ ነው፡፡ የሚመሰረተው በካልዓይ አንቀፅ ላይ ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ አንቀፅ ምሳሌ ነው፡፡

ካሳ እንጨት ል-ይ-ፈልጥ ነው = ሊፈልጥ 4

ምሳሌው፣ ካሳ እንጨት ለመፍለጥ ማቀዱን ያመለክታል፡፡ ይህን የምታመለክተው ምዕላድ የባለቤት አፀፋ የሆነችውን /-ይ/ ቀድማ በመነሻ ላይ ገብታለች፡፡

## ወጣኝ አንቀፅ

የታቀደ ነገር ሳይጀመር አይቀርም፣ ይዋል ይደር እንጅ፡፡ ሲጀመር፣ የድርጊቱ ገላጭ ከሆነው አምድ ቀጥሎ ጀመር የሚል ምዕላድ ይገባል፡፡ ይህም ጀመረ ከሚለው ግስ ጋር ተዛምዶ ይኑረው እንጅ፣ የተለየ ተግባር ያለው አህድ ነው፡፡ ተግባሩ ለወጣኙ አንቀፅ ረዳት መሆን ነው፡፡ ዋናው አምድ የተመሰረተው ከአይነተኛው የካልዓይ አንቀፅ አምድ ላይ ነው፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመለከት፡፡

ከሳ እንጨት ይ-ፈልጥ ጀመር 5

ምሳሌው ድርጊቱ መጀመሩን ብቻ ያመለክታል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ስላለው ሁኔታ የሚነግረን ነገር የለም፡፡ የተጀመረው ድርጊት ሊቀጥል ወይም ሊቋረጥ ይችላል፡፡ የሚቀጥል ከሆነ የተለየ መግለጫ ይኖረዋል፡፡ ይህን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ቀጣይ አንቀፅ

ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ቀጣይ አንቀፅ አንድ የተጀመረ ድርጊት ሳይቋረጥ መቀጠሉን ያመለክታል፡፡ ልዩ ምልክቱ /እይይኧ-/ የሚል ምዕላድ ነው፡፡ መሰረቱ ደግሞ የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ መሳሌ ነው፡፡

ካሳ እንጨት እየ-ፈለጠ ነው 6

አንቀፁ እየፈለጠ የሚለው ነው፡፡ እሱን ተከትሎ የገባው ነው የሚለው ረዳት ግስ ነው፡፡ ተግባሩን በሚቀጠለው ንዑስ ክፍል እናየዋለን፡፡

ድርጊቱ ተቋርጦ ወዲያውኑ ወይም ቆይቶ፣ እንደገና ሊጀምርና ሳይቋረጥ ለተወሰነ ጊዜ ሊቀጥል፣ እንደገናም ሊቋረጥና ደግሞ ሊቀጥል ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለ ድርጊት ደጋጋሚ ይባላል፡፡ የሚደጋገመውም አንድም በድርጊቱ ፈፃሚ ሰው ባህሪ ምክንያት ወይም በድርጊቱ ልዩ ባህሪ ሊሆን የችላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንዳንድ የመጠጥ ሱሰኞች በየምሽቱ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት የሚያደርጉት የመመላለስ ድርጊት የዚህ አይነት ነው፡፡ ድርጊቱ ደጋጋሚ መሆኑን ለመግለፅ የግሱ አምድ ራሱን ይደጋግማል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

ካሳ እዚህ ቤት ሁል ጊዜ ይ-መላለስ-አል 7

ድርጊቱ የአንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ አንቀፁ ይመለስ-አል የሚል የሆናል፡፡

አንዳንዱ ድርጊት በባህሪው ሳያቋርጥ ለተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል ነው፡፡ ለምሳሌ፡ አንድ ሙቀጫ ከከፍተኛ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚያደርገው የመንከባለል እንቅስቃሴ የዚህ አይነት ነው፡፡ ደልዳላ ቦታ ወይም ዳጋፊ እስኪያገኝ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ዳገት የመውጣት ተግባርም እንደዚሁ ጊዜ ፈጅ ነው፡፡ "ወጣ ወጣና እንደ ሽንበቆ፣ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ" እንደሚባለው አይነት ነው፡፡ ሁለቱም አምዶች ደጋጋሚ ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቀጣይ ድርጊቶችን እንደ ዱብ አለ፣ ከሚሉት ቅፅበታዊ ድርጊቶች ጋር በንፅፅር ማየቱ፣ ድርጊቶች አንድ ወጥ እንዳልሆኑ ለመረዳት ያስችላል፡፡ አንቀፅ የምንለውም በመሰረቱ ይህን የድርጊቶችንና የሁነቶችን ውስጣዊ ሁኔታ የሚመለከተውን የግስ ባህሪ ነው፡፡

## ጨራሽ አንቀፅ

ወጣኝ አንቀፅ ድርጊት መጀመሩን እንደሚያመለክት ሁሉ፣ ጨራሽ አንቀፅም አንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ማለቁን ያመለክታል፡፡ አትኩሮቱ ከፍፃሜው ላይ ነው፡፡ ይህን የሚገልፀው አንቀፅ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ቦዝ አንቀፅ የሚባለው ነው፡፡ ቦዝ የሚባልበት ምክንያት ካልዓይ ወይም ቀዳማይ አንቀፅ ካልተከተለው በስተቀር በራሱ ብቻ ጊዜን ለመግለፅ ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህን ከሚከተለው መሳሌ መረዳት የቻላል፡፡

ካሳ እንጨት ፈልጥ-እ ... 8

ይህን የሚሰማ ሰው፣ በርግጥ ፈለጣው ማለቁን ይረዳል፤ ግን ከዚያስ? የሚል ጥያቄ መጠየቁ አይቀርም፡፡ ጥያቄው እንዳይነሳ፣ ሄደ ወይም ይሄዳል የሚል የቀዳማይ ወይም የካልዓይ አንቀፅ ግስ እንዲከተለው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የጨራሽ አንቀፅ መሰረት ካልዓይ አንቀፅ ነው፡፡ በዚህም ከቀዳማይ አንቀፅ ላይ ከሚመሰረተው፣ ከቀጣይ አንቀፅ ይለያል፡፡ በተጨማሪም አምዱን ተከትሎ የሚገባው የባለቤት አፀፋ አገናዘቢ ነው፡፡ ስለዚህም ፈለጥ-ኧ ብሎ፣ ፈልጥ-እ ይላል፡፡

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው አንቀፆች የተለያዩ የድርጊት ባህሪያትን ያመለክታሉ፡፡ ድርጊት መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ መቋዋጨቱንና ከዚያም መፈፀሙን ያመለክታሉ እንጅ መቸነቱን አያመለክቱም፡፡ ይህ የሚገለፀው ጊዜ በሚባለው ሌላ ሰዋሰዋዊ የግስ ባህሪ ነው፡፡ እሱን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ጊዜ

ከፍ ሲል ድርጊቶች በጥቅሉ የተፈፀሙ ወይም ያልተፈፀሙ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ገልፀናል፡፡ ግን እያንዳንዱ ድርጊት የሚታቀድ፣ የሚወጠን፣ የሚቀጥል፣ እናም የሚቋዋጭ ሊሆን እንደሚችልና ይህም ሁኔታ የሚገለፀው በተለያየ የግስ አምድና በተለያዩ ቅጣዮች እንደሆነ ተጠቅሶአል፡፡ የተፈፀሙትም ሆኑ ያልተፈፀሙት ድርጊቶች በጊዜ ይወሰናሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመው የዛሬ አመት ወይም ከዚያ በፊት፣ ወይም ደግሞ የዚያን ያህል ሳይርቅ ከአንድ ደቂቃ በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ ገና ያልተፈፀመ ድርጊትም ፍፃሜ የሚያገኘው ከቅርብ ወይም ከረዥም ጊዜ በሁዋላ ሊሆን ይችላል፡፡ በፊትና በሁዋላ የምንለው ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ተነስተን ነው፡፡ ያ ጊዜ አሁን፣ ከአሁን በፊት ወይም በሁዋላ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያ ጊዜ በፊት የተፈፀመ ድርጊት የሀላፊ ጊዜ ሲባል፣ ከዚያ ጊዜ በሁዋላ የተፈፀመ፣ የትንቢት ጊዜ ድርጊት ይባላል፡፡ እነዚህ ሁለት የጊዜ አይነቶች የሚገለፁት ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የተለያዩ የአንቀፅ አይነቶች መሰረትነትና በተለያዩ ረዳት ግሶች እንዲሁም የጊዜ ተውሳከ ግሶች ነው፡፡ አንቀፆቹ ድርጊቶቹን ሲገልፁ፣ ረዳት ግሶቹና ተውሳከ ግሶቹ ጊዜውን ያመለክታሉ፡፡ ሁኔታውን እያንዳንዱን የጊዜ አይነት እየጠቀስን እንደሚከተለው እናሳያለን[12]፡፡

---

[12] በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ ለማግኘት ጎልደንበርግ (1964)ን ይመልከቱ፡፡

ርባታ

## የሀላፊ ጊዜ

ባለፈ ጊዜ የተፈፀመ ድርጊትን ይገልፃል፡፡ የዋህ፣ የቅርብ፣ እንዲሁም የሩቅ ሀላፊ ተብሎ በሶስት ንዑስ ክፍሎች ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው በቀዳማይ አንቀፅ፣ ሌሎቹ በካልዓይ አንቀፅና በረዳት ግሶች አማካኝነት ይገለፃሉ፡፡

## የዋህ ሀላፊ

አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ብቻ ያመለክታል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ እንበሳ ገደለ 1
(ለ) አስቴር ስኒ ሰበረች

የምሳሌዎቹ ግሶች ቅርፅ የቀዳማይ አንቀፅ ነው፡፡ ግሶቹም የሚያመለክቱትም የድርጊቶቹን መፈፀም ብቻ ነው፡፡ ድርጊቶቹ የተፈፀሙበትን ጊዜ ለይተው አይጠቅሱም፡፡ ጊዜውን ለመወሰን እንደ ትናንት፣ ዛሬ፣ ወዘተ፣ ያሉ የጊዜ ተውሳከ ግሶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የሚከተለውን ሊመስሉ ይችላሉ፡፡

(ሀ) እኔ ትናንት እንበሳ ገደልኩ 2
(ለ) አስቴር ዛሬ ስኒ ሰበረች
(መ) አሁን ስኒ ሰበረች

በዚህም ምክንያት በምሳሌ (1) እንደተጠቀሱት ያሉ አረፍተ ነገሮች አንቀፅ እንጅ በግሀድ የሚታይ የጊዜ ምዕላድ የላቸውም፡፡ ገደልኩ የሚለው አንቀፅ የሚገልፀው ድርጊትም በማንኛውም የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል፡፡ የዋህ የተባለበትም ምክንያት፣ ጊዜውን በውል ለማሳየት ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል፡፡ አንቀፁ ባጠቃላይ ድርጊቱ ያለፈ መሆኑን እንጅ፣ መቼ እንደተፈፀመ ጊዜውን የሚያመለክት ረዳት ግስ የለውም፡፡

## የቅርብ ሀላፊ

አንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ የተፈፀመ መሆኑንና፣ ከተፈፀመም ብዙ ጊዜ ያልቆየ፣ ስለዚህም ያልተረሳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ድርጊቱ የሚገለፀው በጨረሽ አንቀፅ አምድና /-አል/ በሚል ረዳት ግስ አማካኝነት ነው፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

ካሳ እንበሳ ገድል-አ-አል (= ገድሎአል) 3

የግሱ አምድ /ግኽድል-/ የሚል ሲሆን፣ መሰረታዊ ቅርፁም የካልዓይ አንቀፅ ነው:: ከአምዱ ቀጥሎ የሚታየው /-እ/ የባለቤት አፀፋ ነው[13]:: ከእሱ ቀጥሎ የሚታየው /-እል/ የሚለው ረዳት ግስ ነው:: ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን ብቻ ያመለክታል::

እኔ እንበሳ ገድል-ኤ -እለሁ (= ገድያለሁ) 4

በግሱ አምድ ላይ የሚታየው የባለቤት አፀፋ በቀዳማይ አንቀፅ ከሚታየው ተመሳሳይ አፀፋ የተለየ ነው:: የቀዳማይ አንቀፅ የአንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ የባለቤት አፀፋ /-ኩ/ ሲሆን፣ በጨራሽ አንቀፅ አምድ ላይ ግን፣ ይኸው አፀፋ የሚከሰተው /-ኤ/ ሆኖ ነው:: የአፀፋው አይነትና የአምዱ ቅርፅ የአንቀፁን አይነት ይወስናሉ:: አንቀፁም ከላይ እንደተገለፀው፣ ጨራሽ ነው:: /-እል/ የሚለው ረዳት ግስ ከዚህ ጨራሽ አንቀፅ ጋር ሲገባ፣ ድርጊቱ ከተፈፀመ በሁዋላ ብዙ የጊዜ እንዳላለፈ ብቻ ያመለክታል:: የግሱን ውስጣዊ አወቃቀር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል:: 5

| አምድ | አንቀፅ | አፀፋ | ጊዜ | አፀፋ |
|---|---|---|---|---|
| ካልዓይ | ጨራሽ | ዘርፍ | ቅርብ | ባለቤት |
| ስኽብር- | | -ኤ | -እል | -ሁ |

የረዳት ግሱ አፀፋና የአንቀፁ አፀፋ የተለያዩ መሆናቸውን ልብ እንበል:: የአንቀፁ አፀፋ የድርጊቱን ፍፃሜ ብቻ ያመለክታል:: የረዳት ግሱ አፀፋ የባለቤቱን መደብ፣ ቁጥር ወይም ፆታ ይጠቁማል:: በመጨረሻም የአንቀፁ አፀፋዎች ቀደም ሲል በስሞች ርባታ ላይ ካየናቸው የዘርፍ ሙያ አፀፋዎች ጋር አንድ ናቸው፣ ከ/-እ/ በስተቀር:: ይህ አፀፋ በስሞች ላይ /-ኢ/ ሆኖ እንደሚከሰት አይተናል:: ከዚህ ላይ ቅርፁን መለወጡ፣ ከአንቀፁ ጋር ያለውን ቁርኝት ያመለክታል::

## *የሩቅ ሀላፊ*

ከላይ እንዳየነው የቅርብ ሀላፊ ጨራሽ አንቀፅ፣ ይህም አንድ ተፈፅሞ ያለቀ ድርጊትን ያመለክታል:: በዚህና በዚያ መካከል ያለው ልዩነት ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ርቀትና ቅርበት ብቻ ነው:: ይህም ስለድረጊቱ ከምንናገርበት ጊዜ አኳዋያ ሲለካ ነው:: በዚህ ላይ ጊዜው ሩቅ ስለሆነ፣ ከአንቀፁ ጋር የሚዋቀረው ረዳት ግስ ነበር የሚለው ነው:: የዋናው ግስ አምድ አንቀፅ አሁንም ጨራሽ ነው:: የረዳቱ ግስ አንቀፅም ቀዳማይ ነው:: የሁለቱ አንቀፆች ቅንጅት ጊዜውን ሩቅ ያደርገዋል:: በዚህም /-እል/ ከሚለው ረዳት ግስ ጋር ከሚዋቀረው የቅርብ ሀላፊ ጨራሽ አንቀፅ ሲለይ ችሎአል:: ልዩነቱ ግን የጊዜ ብቻ ነው፣ የድርጊት

[13] /-እ/ ሶስተኛው አይነት የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው:: አንደኛው በቀዳማይ አንቀፅ የሚገኘው /-ኧ/ ሲሆን፣ ሁለተኛው በካልዓይ አንቀፅ መነሻ ላይ የሚገኘው /ይ-/ ነው:: /-እ/ ደግሞ በካልዓይ አንቀፅ አምድ መድረሻ ላይ የሚገኝ ነው:: ሁሉም የሶስተኛ መደብ ዘረ-ምዕላዶች ናቸው::

አይደለም፡፡ በድርጊት ደረጃ ሁለቱም ጨራሾች ናቸው፡፡ የግሱን ያቀነጃጀት ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

| <u>አምድ</u> | <u>እንቀፅ</u> | <u>አፀፋ</u> | <u>ረዳት</u> | <u>አፀፋ</u> 6 |
|---|---|---|---|---|
| ካልዓይ | ጨራሽ | ዘርፍ | ነበር | --- |
| ሰኸብር- | | -ኦ | | |

በዚህ መስረት፣ ከላይ በተራ ቁጥር (3) /-አል/ በሚለው ረዳት ግሰ አማካኝነት የተጠቀሰው የቅርብ ሀላፊ አረፍተ ነገር፣ በሩቅ ሀላፊ ጊዜ ሲነገር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ካሳ አንበሳ <u>ገድሉ ነበር</u> 7

<u>ገድሉ</u> የሚለው ግስ መሰረት የካልዓይ እንቀፅ ይሁን እንጅ፣ ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ሀላፊ፣ ከሀላፊም የሩቅ ሀላፊ ነው፡፡ ከዚህም እንቀፅና ጊዜ የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ጊዜው ሀላፊ ሆኖ፣ ድርጊቱ ያላለቀ፣ ስለዚህም እንቀፁ ካልዓይ፣ ሲሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በላይ የተገለፁትን ሶስት የጊዜ አይነቶች እጠቃሎ በሀለፊ ጊዜ ስር ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

## የኢሀላፊ ጊዜ

አንድ ገና ያልተፈፀመ ድርጊት የሚፈፀምበትን የሚሳይ የጊዜ አይነት ነው፡፡ የሚገለፀው ከካልዓይ እንቀፅ አምድ ላይ /-አል/ የሚለውን ረዳት ግስ በመቀጥል ነው፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ እንበሳ ይ-ገድል-ኣል (ይገድላል) 8

/ይ-/ ቀደም ሲል ያየነው የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው፡፡ /-ግኸድል-/ የሚለውን የካልዓይ እንቀፅ አምድ ነው፡፡ ድርጊቱ ገና ያልተፈፀመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ /-አል/ የሚለው ረዳት ግሱ ሲሆን፣ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ጊዜ ያመለክታል፡፡ ይህም ከአሁን ጀምሮ ወደፊት የሚመጣውን የቅረብም ሆነ የሩቅ ጊዜ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ በጣም የቅርብ ሲሆን፣ ከ<u>አሁን</u> ጋር አንድ ይሆናል፡፡ ሲርቅም እንደዚሁ ልዩ ልዩ የመጭ ጊዜ ተውሳከ ግሶችን መጠቀምን ያስከትላል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

(ሀ) ካሳ <u>አሁኑኑ</u> ይ-መጥ-ኣል 9
(ለ) ካሳ <u>አሁን</u> ይ-መጥ-ኣል
(መ) ካሳ <u>ትንሽ ቆይቶ</u> ይ-መጥ-ኣል
(ሰ) ካሳ <u>ከርሞ</u> ይ-መጥ-ኣል

ርባታ

ሁሉም ያልተፈፀመ ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡ ልዩነታቸው ድርጊቶቹ ወደፊት የሚፈፀሙበት ጊዜ፣ ንግግር ከምናደርግበት ጊዜ መራቅና መቅረብ ነው፡፡ ይህም የሚገለፀው በግሱ ቅርፅ ወይም በረዳት ግሱ ሳይሆን፣ በተውሳከ ግሶቹ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በግሳዊ ቅርፁ ከትንቢት ጊዜ የተለየ፣ የአሁን የሚባል የጊዜ አይነት አለመኖሩን ነው፡፡

እስካሁን ያየነው በካልዓይ፣ በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፆች የሚገለፁ ድርጊቶችንና /-አል/ እና ነበር በሚሉ ረዳት ግሶች አማካኝነት የሚገለፁ የጊዜ አይነቶችን ነው፡፡ አንቀፆቹ ያልተፈፀመ፣ የተፈፀመ እና የተጨረሰ ድርጊትን ሲያመለክቱ፣ ጊዜያቱ ድርጊቱ የተፈፀመበት ወይም ያልተፈፀመበት ወይም የተጨረሰበት ወቅት፣ ስለድርጊቱ ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ወይም በሁዋላ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ያለውን ሩቅ ጊዜ፣ ነበር በሚለው፣ ለምንነጋገርበት ጊዜ ቅርብ፣ ወይም ከእሱ ጋር አንድ የሆነውን ጊዜ፣ /-አል/ በሚለው ረዳት ግስ እንገልፃለን፡፡

የአንድ ድርጊት አፈፃፀም ግን ከዚህ ላይ እንደገለፅነው በሰሰት ብቻ ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡ በመፈፀም ላይ ያለና ያላለቀ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ እንደዚሁ ቀጣይ ሊሆን ይችላል፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጊዜው ብቻ ተለይቶ የማያቋርጥ ጊዜ ይባላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ቀጣዩ ጊዜው ብቻውን ሊሆን አይችልም፣ ቀጣዩ ድርጊቱ ነው፣ ሊባል ይችላል፡፡ ጊዜ ያለድርጊት ብቻውን አይታሰብም ማለት ይቻላል፡፡

አንድ ድርጊት ሳይቋረጥ በመፈፀም ላይ የሚገኘው አሁን ወይም ከአሁን በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚሁ መሰረት የማያቋርጥ የአሁን ወይም የሀላፊ ጊዜ ድርጊት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ የድርጊቱን ቀጣይነት ለማመልከት፣ /እይይኸ-/ የሚል ምዕላድ በአምዱ መነሻ ላይ ይገኛል፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ እየ-እነበበ... 10

ይህ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ጊዜ የለውም፡፡ እየ-እነበበ የሚለው የቀጣይ አንቀፅ ግስ ነው፡፡ የሚያመለክተውም፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ አንቀፅን ብቻ ነው፡፡ ጊዜን አያሳይም፡፡ ይህን ለማሳየት ረዳት ግስ ያስፈልገዋል፡፡ የድርጊቱ ቀጣይነት ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ በፊት ከሆነ፣ ነበር የሚል ረዳት ግስ ጋር ይገባል፡፡ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ጋር አንድ ከሆነ፣ ነው ከሚለው ጋር ይገባል፡፡ የድርጊቱ ቀጣይነት ወደፊት የሚታይ ከሆነ፣ ከጊዜ ተውሳከ ግስ ጋር ይገባል፡፡ ይህን ሲያደርግ፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር ግስ የሚከተሉትን ይመስላል፡፡

(ሀ) ካሳ መፅሀፍ እየ-እነበበ ነው (የአሁን) 11
(ለ) ካሳ መፅሀፍ እየ-እነበበ ነበር (የሀላፊ)
(መ) ካሳ [ነገ መፅሀፍ እየ-እነበበ] ይጠብቅሀል... (የትንቢት)

ምሳሌ (መ) ቀጣይ አንቀፅንና የትንቢት ጊዜን ያመለክታል፡፡

ርባታ

<u>ነበር</u> የሚሰው ረዳት ግስ ከካልዓይ አንቀፅ ግስ ጋር ሲገባ፣ ያልተፈፀመና ተደጋጋሚ የሆነ ተግባርን ሊያመለክት ይችላል፡፡ የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

(ሀ) ካሳ በግ <u>ይ-ጠብቅ-ኣል</u> 12

(ለ) አስቴር በወጣትነትዋ እንጨት <u>ት-ሰብር</u> ነበር

ሁለቱም ያልተፈፀመ ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡ የመጀመሪያው ድርጊት ጊዜ፣ አሁንና ወደፊትን ያጠቃልላል፡፡ ወደ ሁዋላም ሊሄድ ይችላል፡፡ ሁለተኛውም እንደዚሁ የአስቴርን የልጅነት ዘመን የሚሸፍን ረዥም ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ረዥም ጊዜ የሚፈጅ ድርጊት ደግሞ ከዕለት ያልፍና የዘወትር ወይም የሰርክ ተግባር ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከጊዜ አንፃር ሀላፊ ወይም ኢ.ሀላፊ ነው፡፡ ሀላፊው የቅርብና የሩቅ፣ ኢ.ሀላፊው የአሁንና የወደፊት የሚሉ ክፍሎች አሉት፡፡ ከአንቀፅ አኳዋያ ድርጊቱ፣ የታቀደ፣ የተጀመረ፣ የቀጠለና የተጨረሰ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ ያለቀ እና ያላለቀ ተብለው፣ እንደ ጊዜው በሁለት ብቻ ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ዋናው ጉዳይ ጊዜና አንቀፅ የተለያዩ፣ ግን ደግሞ የተዛመዱ የግስ ባህሪያት መሆናቸውን መረዳት ነው፡፡

## ስልት

ስልት ከአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ ከቋዋንቋዋ ተግባር ጋር የተቆራኘ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ አንድ አረፍተ ነገር የሚነገረው፣ አንድ የተወሰነ ሀሳብን ለመግለፅ፣ በተገለፀ ሀሳብ ላይ አስተያየት ለመስጠት፣ ጥያቄ ለመጠየቅ፣ ተቃውሞ ለማሰማት፣ ትዕዛዝ ለማስተላለፍ፣ አጥፊን ለመግሰፅ፣ ለመርገም፣ ደግ አድራጊን ለመመረቅ፣ ለማመስገን፣ ለማቆላመጥ፣ ወዘተ፣ ነው፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን ለመግለፅ የምንጠቀምበት የመዋቅር አይነት የተለያየ ነው፡፡ ይህን የተለያየ ተግባር ምንገልፅበት ስርዓት ስልት ይባላል፡፡

ማንኛውም ቋዋንቋዋ የተለያዩ ተግባራትን የሚገልፁ የተለያዩ መዋቅሮች ከምችት ነው፡፡ በየቀኑ የምንለውንና የምንሰማውን ሁሉ ብናሰበው፣ ከዚህ ከምችት የሚወጣና ከእሱም የማይዘል መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለንኒጋገርም የምንፈፅመው በመሰረቱ እነዚህን ልዩ ልዩ ተግባራትን ነው፡፡ መፈፀሚያውም ልዩ ልዩ ቋዋንቋዋ ነው፡፡ መርገሚያው ከመመረቂያው፣ ትዕዛዝ መስጫው ከማለቻው የተለየ ነው፡፡ በተለምዶ ቋዋንቋዋ የሀሳብ መግለጫ መሳሪያ ነው፣ እንላለን እንጅ፣ መሳሪያነቱ ከዚህ ያለፈ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ማንኛውም አረፍተ ነገር ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ አሉታዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ወዘተ፣ እየተባለ እንደ ግብሩ አይነት፣ አንዱ ከሌላው ይለያል፡፡ ልዩነቱ በአብዛኛው የሚታየው በግሱ ላይ ነው፡፡ ልዩነቱ የአምድ ወይም የቅጣይ ሊሆን ይችላል፡፡ ዝርዝሩን እንደሚከተለው በሰንጠረዥ እናሳያለን፡፡

ርባታ

| መደብ | ሁተታዊ | መጠይቃዊ | እሉታዊ | ትዕዛዛዊ/ይሁንታዊ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | እ-ሰብር- | ል-እ-ስበር[14] | እል-ስበር- | | ——— |
| 2ኛ ተ | ት-ሰብር- | ት-ሰብር | አት-ስበር- | <አል-ት-ስበር | ስበር |
| እ | ት-ሰብር-ኢ- | ት-ሰብር-ኢ | አት-ስበር-ኢ- | <አል-ት-ስበር-ኢ | ስበር-ኢ |
| 3ኛ ተ | ይ-ሰብር- | ይ-ስበር | አይ-ስበር- | <አል-ይ-ስበር | ይ-ስበር |
| እ | ት-ሰብር- | ት-ስበር | አት-ስበር- | <አል-ት-ስበር | ት-ስበር |
| | ት-ሰብር-ኡ- | ት-ሰብር-ኡ | አት-ስበር-ኡ- | <አል-ት-ስበር-ኡ | ስበር-ኡ |
| | ይ-ሰብር-ኡ- | ይ-ስበር-ኡ | አይ-ስበር-ኡ- | <አል-ይ-ስበር-ኡ | ይ-ስበር-ኡ |

1 የስልት ሰንጠረዥ

የሁተታዊው ግስ ታሀታይ ቅርፅ /-ሰኧብር-/ ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል ያየነው የካልዓይ አንቀፅ አምድ ነው፡፡ የትዕዛዛዊ ስልት ታሀታይ ቅርፅም /ሰብኧር-/ ሲሆን፣ በሁለቱ አንቀፆች መካከል ያለው ልዩነት አናባቢው /ኧ/ የገባበት ቦታ ነው፡፡ በሁተታዊው ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ ሲገባ፣ በመጠይቃዊ፣ በትዕዛዛዊና በአሉታዊ ስልት ከሁለተኛው ተናባቢ ቀጥሎ ይገባል፡፡

በትዕዛዛዊ ስልት፣ ፆታንና ቁጥርን የሚያመለክቱት ምዕላዶች አምዱን ተከትለው ሲገቡ፣ በመጠይቃዊ ስልት መደብ አመልካች የሆኑት ምዕላዶች ብቻ አምዱን እየቀደሙ ይገባሉ፡፡ መደብ አመልካቾቹ /እ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ ባለቤትን ያመለክታሉ፡፡ ፆታ

---

[14] ቀደም ሲል ስለ አንቀፅ ስንወያይ እንዳየነው፣ /ል-/ የአቃጅ አንቀፅ ምዕላድ ነው፡፡ ይህ አንቀፅ የሚገኘው በ<u>ዕቅፍ</u> አረፍተ ነገር ነው፡፡

[[አስቴር ል-ትሄድ] ነው]

ስንል ድርጊቱ መታቀዱን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም ከአቃጅነት በተጨማሪ የሞይነት ተግባር አለው፡፡ እንደ አቃጅ አንቀፅ፣ መጠይቃዊ ስልትም የሚገለፀው በተራ ሳይሆን፣ በዕቅፍ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፤

ሂድ!

ስንል፣

[እኔ [አንተ ሂድ] ብያለሁ]

ማለታችን ነው፡፡ በዚህ ውስጥ [አንተ ሂድ] የሚለው ትዕዛዝ አንቀፅ ነው፡፡ አገባቡ በዕቅፍነት ነው፡፡ /ል-እ-ሰብኧር-/ የሚለውም እንደዚሁ ነው፡፡ ጉዳዩን በተመለከተ ሀይሉ (1980)ን ይመልከቱ፡፡

አመልከችዋ /-ኢ/ ስተሆን፣ ቁጥር አመልካቾቹ ደግሞ /-ን/ እና /-ኡ/ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አንደኛ መደብን፣ ሁለተኛው ሌሎቹን መደቦች ያመለክታል፡፡ ከዚህ ላይ ቀደም ሲል ስለፆታ ስንወያይ፣ እንሰታይ ፆታ ብቻ በምዕላድ እንደሚገለፅና ከዚህ የተለየ የወል ወይም የግዑዝ ፆታ የሚባል እንደሌለ ገልፀን ነበር፡፡ ከላይ የሚታየው ሰንጠረዥም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

አሉታዊ ስልት የሚገለፀው /አል-/ በሚል ምዕላድ ነው፡፡ አገባቡ መደብ አመልካቹን ምዕላድ እየቀደመ ነው፡፡ በዚህ ምዕላድ መድረሻ ላይ የሚገኘው /ል-/ በአንደኛና በሶስተኛ መደብ ላይ ሲገደፍ፣ በሁለተኛ መደብ ላይ፣ ከመደብ አመልካቹ ምዕላድ ጋር ተመሳስሎ /ት/ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩን በስነ-ድምፅ ውስጥ ስላየነው ከዚህ ላይ አንደግመውም፡፡

እስካሁን ያየነው እንደ ሰበረ ያሉትን ግሶች የርባታ ስርዓት ነው፡፡ የእነዚህ አይነት ግሶች ስርዓት አንድ ወጥ ነው፡፡ ስለዚህም ከአንዱ ግስ የርባታ ሂደት የሌሎቹንም ግሶች ሂደት መተንበይ ይቻላል፡፡ ለዚህ ነው፣ ስርዓቱን በአንድ ግስ አማካኝነት ለማሳየት የሞከርነው፡፡ ሁሉንም ግሶች በተራ እየወሰድን ስርዓታቸውን እንይ ብንል፣ ጊዜም፣ ቦታም አይበቃንም፤ አስፈላጊም አይደለም፡፡ የአንዱ ግስ የርባታ ስርዓት የሌሎቹም ነውና፡፡ የቋንቋዋ ስርዓታዊነት አንዱ መገለጫ ይህ ነው፡፡

የርባታው ስርዓት የተወሰኑ ግሶችን ባህሪ የማይሸፍን ከሆነ፣ የእነሱን በተለየ ሁኔታ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ግሶች በየቋንቋዋው አሉ፡፡ ድርጊትን ሳይሆን በአንድ ቦታ መገኘትን፣ ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር መለወጥን እንዲሁም አንድ ነገር መሆንን ያመለክታሉ፡፡ እነዚህን የሚያመለክቱ ግሶች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ በሁለት ብቻ ተከፍለው፣ የመኖርና የመሆን ግስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ግሶቹም /ነ-/ እና /አል-/ ናቸው፡፡ እነዚህ ግሶች በረዳት ግስነት የተለያየ ጊዜን የመግለፅ ተግባር እንዳላቸው ቀደም ሲል ስለ አንቀፅና ጊዜ ስንወያይ ተመልክተናል፡፡

ረዳት ግሶች በቅርፃቸውም ሆነ በትርጉማቸው ጎደሎ ናቸው፡፡ ይህ በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቋንቋዋ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ከዋና ግሶች የርባታ ስርዓት ያፈነግጣሉ፡፡ እንዴት እንደሚያፈነግጡ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

| ግስ | መደብ | መደብ ፆታ | መደብ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ነ | 1 | ነ-ኝ | ነ-ን |
| | 2ተ | ነ-ህ | ነ-አች-ሁ-ኡ >ናችሁ |
| | እ | ነ-ሀ-ኢ > ነሽ | |
| | 3ተ | ነ-ኡ > ነው | ነ-አች-ኧ-ኡ > ናቸው |
| | እ | ነ-ት-ኢ >ነች | |
| አል- | 1 | አል-ኧሁ | አል-ኧን |
| | 2ተ | አል-ኧህ | አል-አች-ሁ-ኡ > አላችሁ |
| | እ | አል-ኧሀ-ኢ >አለሽ | |
| | 3ተ | አል-ኧ | አል-ኡ > አሉ |
| | እ | አል-ኧት-ኢ >አለች | |

2 የመደብ፣ የቁጥርና ፆታ ሰንጠረዥ

ርባታ

ጊዜ

ሀላፊ — ኢሀላፊ

| ግስ | | የሩቅ | የቅርብ | የቀህ | የአሁን | ትንቢት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነ-<br>ለሆን- | 1 | ሆን-የ ነበር<br>ሆኘ ነበር | ሆን-የ-እለ-ሁ<br>ሆኛለሁ | ነበር-ሁ | ነ-ኝ | አ-ሆን-እለ-ሁ<br>እሆናለሁ |
| | 2ተ | ሆን-ኸህ ነበር<br>ሆነህ ነበር | ሆን-ኸሁ-አል<br>ሆነሀል | ነበር-ሀ | ነ-ሀ | ት-ሆን-እለ-ሀ<br>ትሆናለህ |
| | ሴ | ሆን-ኸሁ-ኢ ነበር<br>ሆነሽ ነበር | ሆን-ኸሁ-ኢ-አል<br>ሆነሻል | ነበር-ሁ-ኢ-<br>ነበርሽ | ነ-ሁ-ኢ<br>ነሽ | ት-ሆን-ኢ-እለ-ሁ-ኢ<br>ትሆኛለሽ |
| | 3ተ | ሆን-እ በር<br>ሆኖ ነበር | ሆን-እ-አል<br>ሆኖአል | ነበር-ኧ<br>ነበር | ነ-ኡ<br>ነው | ይ-ሆን-አል<br>ይሆናል |
| | ሴ | ሆን-አ በር<br>ሆና ነበር | ሆን-አ-እለ-ት-ኢ<br>ሆናለች | ነበር-ኧት-ኢ<br>ነበረች | ነ-ኧት-ኢ<br>ነች | ት-ሆን-እለ-ት-ኢ<br>ትሆናለች |
| | ብ | ሆን-ን ነበር<br>ሆነን ነበር | ሆን-ን-እለ<br>ሆነናል | ነበር-ን<br>ነበርን | ነ-ን<br>ነን | ዕ-ን-ሆን-እለ-ን<br>ዕንሆናለን |
| | | ሆን-አች-ሁ-ኡ ነበር<br>ሆናችሁ ነበር | ሆን-አች-ሁ-ኡ-አል<br>ሆናችሁአል | ነበር-አች-ሁ-ኡ<br>ነበራችሁ | ነ-አች-ሁ-ኡ<br>ናችሁ | ት-ሆን-እለ-አች-ሁ-ኡ<br>ትሆናላችሁ |
| | | ሆን-ኧ-ኡ ነበር<br>ሆነው ነበር | ሆን-ኧ-ኡ-አል<br>ሆነዋል | ነበር-ኡ<br>ነበሩ | ነ-አች-ኧ-ኡ<br>ናቸው | ይ-ሆን-አል-ኡ<br>ይሆናሉ |
| አለ/<br>ኖር | 1 | ኖር-የ-ነበር<br>ኖሬ ነበር | ኖር-የ-እለ-ሁ<br>ኖሬአለሁ | ነበር-ሁ | አለ-ሁ | አ-ኖር-አለ-ሁ<br>እኖራለሁ |
| | 2ተ | ኖር-ኸሀ-ነበር<br>ኖረህ ነበር | ኖር-ኸሀ-አል<br>ኖረሀል | ነበር-ሀ | አለ-ሀ | ት-ኖር-አለ-ሀ<br>ትኖራለህ |
| | ሴ | ኖር-ኸሽ-ነበር<br>ኖረሽ ነበር | ኖር-ኸሽ-አል<br>ኖረሻል | ነበር-ሽ | አለ-ሽ | ት-ኖር-ኢ-አለ-ሽ<br>ትኖሪአለሽ |
| | 3ተ | ኖር-ኦ-ነበር<br>ኖሮ ነበር | ኖር-ኦ-አል<br>ኖሮአል | ነበር-ኧ | አለ-ኧ | ይ-ኖር-አል<br>ይኖራል |
| | ሴ | ኖር-አ-ነበር<br>ኖራ ነበር | ኖር-አ-አለች<br>ኖራለች | ነበር-ኧች | አለ-ኧች | ት-ኖር-አለ-ኧች<br>ትኖራለች |
| | ብ | ኖር-ኧን-ነበር<br>ኖረን ነበር | ኖር-ኧን-አል<br>ኖረናል | ነበር-ን | አለ-ን | እን-ኖር-አለ-ን<br>እንኖራለን |
| | | ኖር-አችሁ-ነበር<br>ኖራችሁ ነበር | ኖር-አችሁ-አል<br>ኖራችሁአል | ነበር-አችሁ | አለ-አችሁ | ት-ኖር-አለ-አችሁ<br>ትኖራላችሁ |
| | | ኖር-ኧው-ነበር<br>ኖረው ነበር | ኖር-ኧው-አል<br>ኖረዋል | ነበር-ኡ | አል-ኡ | ይ-ኖር-አል-ኡ<br>ይኖራሉ |

3 የጊዜ ሰንጠረዥ

ርባታ

ሰልት

| ግስ | መደብ | ሁተታዊ | መጠይቃዊ | አሉታዊ | ትዕዛዛዊ/ይሁንታዊ |
|---|---|---|---|---|---|
| ነ-/ሆን | 1 | ነ-ኝ | ል-ሁን | አል-ሆን | ል-ሁን<br>ልሁን |
| | 2ተ | ነ-ህ | ት-ሆን | አል-ት-ሆን<br>አትሆን | ሁን |
| | አ | ነ-ህ-ኢ<br>ነሽ | ት-ሆን-ኢ<br>ትሁኝ | አል-ት-ሆን-ኢ<br>አትሆኝ | ሁን-ኢ<br>ሁኝ |
| | 3ተ | ነ-ው | ይ-ሁን | አል-ይ-ሆን<br>አይሆን | ይ-ሁን<br>ይሁን |
| | አ | ነ-ት-ኢ<br>ነች | ት-ሁን | አል-ት-ሆን<br>አትሆን | ት-ሁን<br>ትሁን |
| | ብ | ነ-ን | እ-ን-ሁን | አል-ን-ሆን<br>አንሆን | እ-ን-ሁን<br>እንሁን |
| | | ነ-አች-ህ-ኡ<br>ናችሁ | ት-ሆን-ኡ | አል-ት-ሆን-ኡ<br>አትሆኑ | ሁን-ኡ<br>ሁኑ |
| | | ነ-አች-ኧ-ኡ<br>ናቸው | ይ-ሁን-ኡ | አል-ይ-ሆን-ኡ<br>አይሆኑ | ይ-ሁን-ኡ<br>ይሁኑ |
| አል-/ኖር | 1 | አል-ኧሁ<br>አለሁ | ል-ኑር | አል-ኑር | ል-ኑር |
| | 2ተ | አል-ኧህ<br>አለህ | ት-ኖር | አል-ት-ኖር<br>አትኖር | ኑር |
| | አ | አል-ኧህ-ኢ<br>አለሽ | ት-ኖር-ኢ | አል-ት-ኖር-ኢ<br>አትኖሪ | ኑር-ኢ<br>ኑሪ |
| | 3ተ | አል-ኧ<br>አለ | ይ-ኑር | አል-ይ-ኑር<br>አይኖር | ይ-ኑር |
| | አ | አል-ኧት-ኢ<br>አለች | ት-ኑር | አል-ት-ኖር<br>አትኖር | ት-ኑር |
| | ብ | አል-ኧን<br>አለን | እ-ን-ኑር<br>እንኑር | አል-ን-ኖር<br>አንኖር | እ-ን-ኑር<br>እንኑር |
| | | አል-አችች-ሀ-ኡ<br>አላችሁ | ት-ኖር-ኡ<br>ትኖሩ | አል-ት-ኖር-ኡ<br>አትኖሩ | ኑር-ኡ<br>ኑሩ |
| | | አል-ኧ-ኡ<br>አሉ | ይ-ኑር-ኡ<br>ይኑሩ | አል-ይ-ኖር-ኡ<br>አይኖሩ | ይ-ኑር-ኡ<br>ይኑሩ |

4 የሰልት ሰንጠረዥ

ከመዘርዘሩ እንደሚታየው፣ /ንኽ-/ የሚለው ምዕላድ ጊዜያትንና ስልቶችን የሚያሳየው ሆን (/ሀኦን-/) በሚለው የመሆን ግስ አማካኝነት ነው። /እል-/ የሚለውም እነዚህን ባህሪያት የሚገልፀው ኖር (/ንኦር-/) በሚለው የመኖር ግስ አማካኝነት ነው። ለዚህም ምክንያቱ /ንኽ-/ እና /እል-/ ረዳት ግሶች በመሆናቸውና በቅርፅም ሆነ በትርጉም ከመደበኛ፣ ማለትም ከዋና ግሶች በመለየታቸው ነው። ለምሳሌ፣ /ንኽ-/ ምንም አይነት ትርጉም የለውም። ስለዚህም ባዶ ምዕላድ ነው። ባዶ ቅል እንደማለት ነው፤ ይዘት የለውምና። በቅርፁም እንደ ሰበረ አይነት ግሶች ሶስት ተናባቢ እግር የለውም። ጎደሎ ነው። ስለዚህም የርባታ ስርዓቱ ከመደበደኛ ግስ የተለየ ነው።

ቅጣይ የሚያሳየው ለመደብ፣ ለቁጥር ወይም ለፆታ ብቻ ነው። መደብን የሚያመለክተው ግን በተሳቢ አፀፋ ነው። ይህም እንደ ሰበረ ካሉ ግሶች ስርዓት የተለየ ነው። ምክንያቱም እንደ ሰበረ ያሉ ግሶች የባለቤትን መደብ የሚያመለክቱት በባለቤት አፀፋ ስለሆነ ነው። የተሳቢ አፀፋ መታየት ያለበት ከሳቢ ግስ ጋር ለሚዋቀር ተሳቢ ለማዊ ሀረግ ነው። /ንኽ-/ ሳቢ ግስ አይደለም። የድርጊትም አይደለም፤ የመሆን ነው።

/እል-/ የሚለው ግስም እንደ /ንኽ-/ ጎደሉ ነው። ግን ይዘት አለው። እንደ ጊዜና ስልት ያሉትን ተግባራት የሚገልፀው በአብዛኛው ኖር (/ንኦር-/) በሚለው ግስ አማካኝነት ነው። ይሁን እንጅ፣ አፀፋዎቹ /ንኽ-/ በሚለው ግስ እንደሚታዩት፣ የተባቢ አይደሉም፤ የባለቤት ናቸው። /ንኽ-/ም ሆነ /እል-/ በራሳቸው ቅርፀ የሚከሰቱት በሀትታዊ የአሁን ጊዜ ብቻ ነው።

/ንኽ-/ እና /እል-/ ከሰበረ አይነት ግሶች በቅርፃቸውም ሆነ በተግባራቸው የተለዩ ናቸው። እንደ ሰበረ ያሉት ድርጊትን ሲያመለክቱ፣ እነዚህ ኑረትን ወይም ሁነትን ያመለክታሉ። ሁለተኛም እንደ ሰበረ ያሉ ግሶች ባለ ሶስት ተናባቢ ሲሆኑ፣ እነዚህ ባለ አንድ ተናባቢ ናቸው። /ንኽ-/ የሚለው ግስ ተናባቢ ድምፅ /ን/ ብቻ ነው። /እል-/ የሚለውም እንደዚሁ /ል/ ብቻ ነው። ለዚህም ምክንያት ከሶስቱ ተናባቢዎቹ መካከል ሁለቱን ስለጎረደ ነው። ተናባቢዎቹ /ሀ-ል-ው/ እንደሆኑ ባለፈው ክፍል ተገልፆአል። ተናባቢያቸውን የሚጥሉ ግሶች በጥቅሉ ጎራጅ ግሶች ይባላሉ።[15]

የእንደዚህ አይነት ጎራጅ ግሶች ባህሪ ጎራጅ ያልሆኑ እንደ ሰበረ ያሉ ግሶች የሚከተሉትን የርባታ ስርዓት ለመከተል አለመቻል ነው። ብዚህም ምክንያት ህጉ-ወጥ በመባል ይታወቃሉ። የ/ንኽ-/ እና የ/እል-/ አሉታዊ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ /አይድኽል-/ እና የለ- /ይኽልልኽ-/ የሚል አምድ ነው። አምዱ ላይ የተለያየ የመደብ፣ የፆታ ወይም የቁጥር ምዕላድ ይጨምራሉ። ይህ ሲሆን ለምሳሌ፣ የአንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አሉታዊ ቅርፅ አይደለሁም (/አይድኽልልኽሀኡም/) እና የለሁም (/ይኽልልኽሀኡም/) የሚል ይሆናል።

---

[15] የጎራጅ ግሶችን ባህሪ በተመለከተ ባየ(1997፣ 1999፣ 2004፣) ይመልከቱ።

ርባታ

ሌላው የነዚህ ግሶች ባህሪ ከአግባባቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአንድ በኩል እንደ ማንኛውም ግስ ራሳቸውን ችለው ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ ይህን ወደፊት በሰፊው እናየዋለን፡፡ ለጊዜው ግን የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) [ጎበዝ ነው] 1
(ለ) [ቤት ውስጥ አለ]

እዚህ ላይ ግሶቹ በዋና ግስነት ገብተዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ እነዚሁ ግሶች ለሌሎች ግሶች ረዳት በመሆን ጊዜን ሲያመለክቱ ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ለምሳሌ፣ ሰብሮ-አል እና እየሰበረ ነው ስንል፣ አል እና ነው፣ ሰብሮ እና እየሰበረ የሚሉት የተጣይና የጨራሽ እንቀፅ ግሶች ረዳት ሆነው በመግባት ጊዜን ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ምድባቸው ከግብር ቃላት ጋር ነው፡፡ ግብራቸውም ጊዜን ማሳየት ነው፡፡

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከትነውን እናጠቃልው፡፡ የተመለከትነው የስሞችን፣ የቅፅሎችንና የግሶችን የርባታ ስርዓት ነው፡፡ ሌላው ሊታይ የሚገባው ስርዓት የተውሳከ ግሶች ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ በፊት እንዳየነው፣ ክፍሉ የግብር እንጂ የቃል ክፍል አይደለም፡፡ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት የሚገለፁት በአብዛኛው በመስተዋድድ ሀረጎች ነው፡፡ አንዳንድ ተውሳከ ግስ ሊባሉ የሚችሉ ቃላት ቢኖሩም፣ የርባታ ስርዓት የላቸውም፡፡ ለምሳሌ ክፉኛ የሚለው ቃል ክፉ ከሚለው ቅፅል ላይ የተመሰረተ የሁኔታ ተውሳከ ግስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንደ ቅፅሎች ቅጥዮችን እየጨመረ ወይም ከተናባቢዎቹ መካከል አንዱን ወይም ሌላውን እየደገመ ቅርፁን ሲለውጥ አይገኝም፡፡

ከላይ እንደተገለፀው፣ በዚህ ክፍል ያተኮርነው በስሞች፣ በግሶችና በቅፅሎች የርባታ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ስሞች ለቁጥር፣ ለፆታ፣ ለሙያና ለዕምርነት የተለያዩ ቅጥዮችን እንደሚያስከትሉ አይተናል፡፡ ቁጥርን በሚመለከት፣ /-ኦች/ የብዙነት ሳይሆን፣ የጥቂትነት ምዕላድ እንደሆነ አይተናል፡፡ በመስተዓምሮች ላይ እነ (/እንገኧ-/) ሆኖ በአጉዋዳኝነት ይከሰታል፡፡ ብዛት የሚገለፀው በምዕላድ ሳይሆን በሀረግ ነው፡፡ ይኸውም እንደ መዓት፣ ጅንድ እና ሁሉ ያሉ የመጠን ቃላትን ከነጠላ ስሞች ጋር በመጠቀም ነው፡፡ ይህም ለምሳሌ፣ መዓት በግ፣ በማለት ነው፡፡ አንዳንድ ከግዕዝ የተወረሱ ስሞች ቁጥርን በግዕዙም ሆነ በአማርኛው ስርዓት ያሳያሉ፡፡ ፆታ ተባዕታይና አንስታይ ብቻ እንደሆነና አንስታዩ ብቻ /ኢ-(ት)/ /-አ/ በሚል ምዕላድ እንደሚገለፅ ተገንዝበናል፡፡ የዕምርነት ምዕላዱም /ኡ-/ ሲሆን፣ /-ኧ/ ከሚለው የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ጋር ሲዋሀድ /-ዋ/ እየሆነ እንደሚከሰት አይተናል፡፡

ግሶች መደብ፣ ቁጥር እና ፆታ አመልካች የሆኑ ምዕላዶችን እንደሚያስዙ አይተናል፡፡ መደብ አመልካቾቹ የግሱን እምድ ቀድመው ወይም ተከትለው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ይህም በግሱ የእንቀፅ አይነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እንቀፁ ቀዳማይ ሲሆን፣ ቅጥዮቹ እምዱን ይከተላሉ፣ እንቀፁ ካልዓይ ሲሆን ይቀድማሉ፡፡ በቀዳማይ እንቀፅ የመደብና የቁጥር ወይም የመደብና የፆታ ምዕላዶች ተዋህደው ይገኛሉ፡፡ በካልዓይ እንቀፅ እነዚሁ ምዕላዶች ተለያይተው

ይታያሉ፡፡ መደብ አመልካቾቹ /ሕ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ ሲሆኑ፣ ቁጥር አመልካቾቹ ደግሞ /-ን-/ /-ኡ-/ ናቸው፡፡

ሁለት አይነተኛና አራት መሰስተኛ እንቀፆችን አይተናል፡፡ እነሱም አቃጅ፣ ወጣኝ፣ ቀጣይና ጨራሽ ናቸው፡፡ ቀጣዩ ከቀዳማይ እንቀፅ፣ ሌሎቹ ከካልዓይ እንቀፅ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ቀጣዩ ብቻ አገናዛቢ የባለቤት አፀፋ ያስከትላል፡፡

ግሶች ጊዜንና ስልትን ለመግለፅ በየእንቀፁ ላይ ቅጣዮችንና ወይም ረዳት ግሶችን ያስከትላሉ፡፡ እንቀፆቹ የድርጊቱን አይነት ያሳያሉ፡፡ ረዳት ግሶቹ /አል-/፣ /ንኧ-/ እና ነበር የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቱ የተፈፀመበትን ጊዜ ያሳያሉ፡፡ ይሁን እንጅ፣ እንደ ዋና ግስ ሆነው ይረባሉ፡፡ ሲረቡ፣ እንደ ሰበረ ያሉ ግሶች ከሚከተሉት የርባታ ስርዓት በመጠኑ ያፈነግጣሉ፡፡ ይህ የሚታየው በተለይ /ንኧ-/ በሚለው ረዳት ግስ ነው፡፡ ይህ ግስ የሚያስከትለው ቅጣይ አፀፋ የተሳቢ ነው፡፡ ሁለተኛም የመደበኛ ግሶች አሉታዊ ምዕላድ /አል-/ ሲሆን፣ የረዳት ግሶቹ፣ የአለ እና የነው ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የለም እና አይደለም ነው፡፡ በዚህም ይህን ክፍል እንሰናበታለን፡፡

## መልመጃ

1. መደብ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ከሚኖረው ሚና ጋር የተያያዘ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ፡፡
2. የመደብ ምዕላዶች ቅርፅ ከእንቀፅ አይነት ጋር እንዴት እንደሚያያዝ በምሳሌ ይግለፁ፡፡
3. የፆታ ምዕላዶች ቅርፅ እንደየቃል ክፍሉ ይለያያል፡፡ ምዕላዶቹን እየጠቀሱ ከየቃል ክፍሉ ምሳሌ ይስጡ፡፡
4. ሁለቱን ዋና ዋና የእንቀፅ አይነቶች ስም ይጥቀሱና ለእያንዳንዳቸው ሁለት ምሳሌ ይስጡ፡፡
5. የቀጣይና የጨራሽ እንቀፅን ባህሪ ይግለፁ፡፡
6. /-እችች/ የሚለው ምዕላድ የብዙ ቁጥር መግለጫ አይደለም፣ የተባለበትን ምክንያት ከነማስረጃው የግለፁ፡፡
7. ቀጫጭን የሚለው ቃል ቀጭን ከሚለው ላይ እንዴት እንደተመሰረተ ዘርዝረው ያስረዱ፡፡
8. የቀዳማይ እንቀፅ እምድ ሊያስከትል የሚችለውን የምዕላድ አይነትና መጠን ይግለፁ፡፡
9. የመደብና የፆታ ምዕላዶች በአንድ ቅርፅ የሚከሰቱት በምን እምድ ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡
10. በጊዜና በእንቀፅ መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡
11. ሰበረ እና ሰብሮአል በእንቀፅና በጊዜ እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ ያስረዱ፡፡
12. የአማርኛ ግሶች የ"ሀ" እና የ"ለ" ተብለው የሚከፈሉበትን ምክንያት ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡

# ምስረታ

ባለፈው ንዑስ ክፍል የሶስቱን ዋና ዋና የቃላት ክፍሎች የርባታ ስርዓት ተመልክተናል፡፡ በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራትን ለማመልከት የተለያዩ ቅጥዮችን በማስቀደም፣ በማስከተል፣ እንዲሁም ራሳቸውን በከፊል ወይም በሙሉ በመድገም ቅርፃቸውን በከፊል ሲለዋውጡ አይተናል፡፡ በዚህም የርባታ ስርዓት የአንዱ ክፍል ቃላት ከሌላው ክፍል ቃላት በቅርፃቸው እንዴት እንደሚለዩም ለማሳየት ሞክረናል፡፡

ስርዓቱ በየክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ለተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራት ቅርፃቸውን እንዴት እንደሚለዋውጡ እንጅ፣ እንዴት እንደሚመሰረቱ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ያለውን የሚቀያይር እንጅ፣ አዳዲስ ቃላትን የሚፈጥር ስርዓት አይደለም፡፡ ቅርፅ መቀያየር የቃላት አንደኛው ባህሪ ነው፡፡ ሌላው ባህሪ ለአዳዲስ ቃላት ምስረታ መሰረት መሆን ነው፡፡ ይህን ሲያደርጉ የሚከተሉት ራሱን የቻለ ስርዓት አለ፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው ይህን ስርዓት ነው፡፡

ካሁን በፊት እንዳደረግነው ሁሉ፣ አሁንም እያንዳንዱን የቃላት ክፍል በየተራ እየወሰድን ለአዳዲስ ቃላት ምስረታ እንዴት መሰረት ሊሆን እንደሚችልና የነባር ቃላትንም ውስጣዊ አቀነጃጀት ለማየት እንዴት እንደሚረዳ እንመረምራለን - ከመሰተዋድድና ከመሰተዓምር በስተቀር፡፡ እነዚህን የማናይበት ምክንያት በውስጣቸው የሚገኙት ቃላት ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ክፍል ቃላት መሰረት ሊሆኑ የማይችሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል እንደተገለፀው፣ የነዚህ ክፍሎች ቃላት ይዘት ወይም ፍሬ የላቸውም፡፡ ስለዚህም ሊረቡና ሊራቡ አይችሉም፤ መሀን ናቸው፡፡ ይዘት ባላቸው ክፍሎች ውስጥ የሚገኘው የቃላት መጠን ሲጨምር፣ የእነሱ አይጨምርም፡፡ ባለፉት አስርት አመታት አያሌ ስሞች፣ ግሶችና ቅፅሎች ተፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ በደርግ ዘመን እንደ ስኬት፣ ፍንዳታ፣ ቆይታ፣ ጭምብል፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞች ተፈጥረዋል፡፡ አሁን ደግሞ እንደ ወገነ፣ አመከነ፣ ተገበረ፣ ያሉ ግሶችና እንደ ሙሰና፣ ተሞክሮ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞች፣ እንዲሁም እንደ ጨለምተኛና ዘገምተኛ ያሉ ቅፅሎች ብቅ ብቅ ብለዋል፡፡ ቀደም ሲልም ሆነ አሁን፣ አንድም መሰተዋድድ ወይም መሰተዓምር የሆነ ቃል አልተፈጠረም፤ በውሰትም ከሌላ ቋንቋ አልገባም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው መሰተዋድዶችና መሰተዓምሮች የግብር እንጅ የይዘት ቃላት አለመሆናቸው ነው፡፡ ግብራቸውም ውስን ስለሆነ መጠናቸውም እንደዚሁ ውሱን ነው፡፡


ባለፈው ክፍል እንደተጠቀሰው፣ እንደመሰተዋድድ ያለ ቃል ሁሉ በራሱ ይህ ነው የሚባል ትርጉም የለውም፡፡ ከስሙ እንደምንረዳው፣ የመሰተዋድድ ተግባር ይዘት ያላቸው ቃላት እየተዋቀሩ ሀረግ ሲመሰርቱ የሚፈጥሩትን መዋቅራዊ ዝምድና ማሳየት ነው፡፡ ለምሳሌ፣

የሚለውን መዋቅር ብንመለከት፣ እንደ የሚለው መስተዋድድ የንጋት ኮከብ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ ስማዊ ሀረጉ ከሌላ ካልተጠቀሰ ነገር ጋር የሚነፃፀር መሆኑን የሚገልፅ ቃል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለስማዊ ሀረጉ የሚያበረክተው የትርጉም አስተዋፅዖ የለውም፡፡ የሀረጉ ትርጉም የተመሰረተው ንጋት እና ኮከብ በሚሉት የይዘት ቃላት ላይ ብቻ ነው፡፡ እንደ የሚለው መስተዋድድ ንፅፅርን የማሳየት ተግባር ብቻ ያለው የግብር ቃል ነው፡፡ ስለዚህም ለአዳዲስ ቃላት መሰረት ወይም ዘር ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ክፍል የምናተኩረው እንደ ኮከብ እና ንጋት ባሉ የይዘት ቃላት ላይ ነው፡፡

ትኩረታችን በሁለት ወገን ነው፡፡ በአንድ በኩል የምናውቃቸውን፣ ማለትም የነባር ቃላትን፣ ውስጣዊ አቀነጃጀት ማየት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የአቀነጃጀቱ ስርዓት የማናውቃቸውን አዳዲስ ቃላት እንዴት እንደሚፈጥር መረዳት ነው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ገና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ፅንሰ-ቃላት በእያንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ልሳነ ተፈጥሮ ውስጥ እንዳሉ ገልፀን ነበር፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቃላትን ለአብነት ያህል በዚህ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ለማየት እንሞክራለን፡፡ በስሞች እንጀምራለን፡፡

## *ውልድ ስሞች*


ሁለት አይነት ስሞች አሉ፡፡ አንደኛው እንደ ቤት፣ ሰው፣ ሴት፣ በግ፣ ልጅ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን የያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደ ሰውነት፣ ሴትነት፣ ልጅነት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን የሚያካትት ነው፡፡ የመጀመሪያው አይነት ስሞች ከፎኒሞች የተመሰረቱ ነፃ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ምዕላዶች ይባላሉ፡፡ ለምሳሌ *ቤት* የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ /ብ/፣ /ኤ/ እና /ት/ ከሚሉት ሁለት ተናባቢና ከአንድ አናባቢ ድምፅ የተፈጠረ ባለአንድ ቀለም ምዕላድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አፈጣጠሩ ባለፈው ክፍል ባየነው የቋንቋዋው የቀለም አወቃቀር ስርዓት መሰረት ሲሆን፣ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡




2

ሁለቱ ተናባቢ ድምፆች አናባቢውን ማዕከል አድርገው መዋቅሩን እንደፈጠሩ በግለፅ ይታያል፡፡ በስነ-ድምፅ ደረጃ መዋቅሩ ቀለማዊ ሲሆን፣ በስነ-ምዕላድ ደረጃ ምዕላዳዊ ነው፤ ትርጉም ስላለው፡፡

ይህ ምዕላድ ከሌላ ጥገኛ ከሆነ ምዕላድ ጋር በመዋቀር ቃል ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ /-እኘኘእ/ የሚል ምዕላድ እንዲከተለው ብናደርግ፣ *ቤተኛ* የሚል ቃል ይሰጠናል፡፡ የሁለቱ አወቃቀርም እንደሚከተለው ነው፡፡




3

ሁለቱ ምዕላዶች ተዋቅረው *ቤተኛ* የሚል ቃል መስርተዋል፡፡ ይህ ቃል የሁለት ምዕላዶች ውጤት ስለሆነ፣ ስነ-ምዕላዳዊ ቃል ተብሉ፣ ከፍ ሲል ካየነው ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ምዕላድ ይለያል፡፡ በዚህም መሰረት ከፎኒሞች የሚዋቀሩትና፣ እንደ <u>ቤት</u> ያሉት ነባር፤ ከምዕላዶች የሚዋቀሩት እንደ <u>ቤተኛ</u> ያሉት ደግሞ ውልድ ስሞች ይባላሉ፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው ምዕላድ ከምዕላድ ወይም ከቃል ጋር እየተቀናጀ ቃላት የሚፈጥርበትን ስርዓት ነው፡፡ ወደ ዝርዝር የምስረታው ሂደት እንግባ፡፡

ውልድ ስሞች ከስም፣ ከቅፅል እና ከግስ ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች እንዴት እንደሚወለዱ ከስም ከሚወለዱት በመጀመር ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ስሞች ለሌሎች ስሞች ወላጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ከፍ ሲል ነባር ስሞች ያልናቸው ናቸው፡፡ ከነሱ የሚወለዱ ስሞች የረቂቅ ስሞች ናቸው፡፡ በአይን የማይታይ ባህሪን ያመለክታሉ፡፡ ሁለት አይነት የረቂቅ ስሞች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አይነት ከነባር ስሞች ላይ /-ነነእት/[1] የሚል ምዕላድ ሲጨመር የሚወለዱ ስሞችን የያዘ ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን፡፡

---

[1] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ፡፡ ለአቀራረብ እንዲቀል፡ በዚህ ክፍል የሚሰጡት ምሳሌዎች በሙሉ፡ ሁኔታ ካላስገደደ በስተቀር፣ በመደበኛው ስርዓተ ፅህፈት ይፃፋሉ፡፡ ቅጥይ ምዕላዶቹ ብቻ በፎኒማዊ አፃፃፍ በእዝባር ውስጥ ይፃፋሉ፡፡

| ነባር ስም | ውልድ ስም | | 4 |
|---|---|---|---|
| ሰው | ሰው-ነት | ሰውነት | |
| ልጅ | ልጅ-ነት | ልጅነት | |
| ሴት | ሴት-ነት | ሴትነት | |

የዚህ አይነት ስሞች ከስም ብቻ ሳይሆን፣ ከቅፅልም ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

| ቅፅል | ስም | | |
|---|---|---|---|
| ደግ | ደግ-ነት | ደግነት | 5 |
| ጥሩ | ጥሩ-ነት | ጥሩነት | |
| ብልህ | ብልህ-ነት | ብልህነት | |
| ቸር | ቸር-ነት | ቸርነት | |

የነዚህን ሁለት አይነት የረቂቅ ስሞች የአፈጣጠር ስርዓት እንደሚከተለው አጠቃሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 1፣

[{ስም፣ቅፅል }] + [–ነት] ⟶ [ ስም]
የረቂቅ

ስርዓቱ፣ ከስም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንንኧት/ የሚል ምዕላድ ሲጨምር፣ የረቂቅ ስም እንደሚፈጠር ያሳያል፡፡ ይህ እይነት ስም የሚመሰረተው በ/–ንንኧት/ አማካኝነት ስለሆነ፣ይህን ቅጣይ የረቂቅ ስም መስራች ምዕላድ እንለዋለን፡፡ ምዕላዱ በስሙ ወይም በቅፅሉ መድረሻ ላይ ተቀጥሎ ስለሚገባም ተከታይ ምዕላድ ይባላል፡፡ ይህን የአመሰራረት ስርዓት በመከተል ከማንኛውም ቅፅል ወይም ስም ላይ የረቂቅ ስም መመስረት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡ <u>ውብ</u> ከሚለው ቅፅል ላይ /-ንንኧት/ን ብንጨምር፣ <u>ውብነት</u> የሚል ስም እናገኛለን፡፡ ይህም <u>ውበት</u> ከሚለው በቅርፁ የተለየ ነው፡፡ ከውበት ጋር ተዛምዶ ላለው አዲስ ፅንሰ-ሀሳብ ስያሜ ሊሆን ይችላል፡፡ <u>የውብነትዋ</u> ደረጃ እስከምን ድረስ ነው ብንል? <u>የውበትዋ ደረጃ</u> እስከምን ድረስ ነው? ከሚለው ጋር አንድ አይመስልም፡፡

ሁለተኛው የረቂቅ ስሞች አይነት ከውልድ ስሞች፣ ከነፃ ወይም *<u>ዕስር</u>* ቅፅላዊ አምዶች ላይ / ̲ኧት/ የሚል ምዕላድ በመጨመር የሚፈጠሩ ስሞችን ያጠቃልላል፡፡ ወደ ዝርዝር ሁኔታው ከመግባታችን በፊት፣ ምናልባት <u>አምድ</u> የሚለውን ቃል ከዚህ ላይ መግለፁ ተገቢ ይሆናል፡፡ ቃሉን ቀደም ሲል በተደጋጋሚ የጠቀስነው ቢሆንም፣ ምንም አይነት ግላዬ አልሰጠነውም፡፡

ማንኛውም ዕስር ምዕላድን ሊያስቀጥል የሚችል ነፃ ወይም ዕስር አሀድ <u>አምድ</u> ይባላል፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ስም</u> | <u>ስም</u> | | |
| ክብር | ክብረ-ኧት | ክብረት | 6 |
| ሹም | ሹም-ኧት | ሹመት | |
| <u>ቅፅል</u> | <u>ስም</u> | | |
| ብስል | ብስል-ኧት | ብስለት | |
| ቅርብ | ቅርብ-ኧት | ቅርበት | |
| ብልጥ | ብልጥ-ኧት | ብልጠት | |
| ዕውቅ | ዕውቅ-ኧት | ዕውቀት | |

ከዚህ በላይ የሚታዩት ውልድ ስሞች ከነፃ ስማዊና ቅፅላዊ አምዶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የሚታዩት ደግሞ ከዕስር አምዶች ላይ ይህንኑ ምዕላድ በማስከተል የተመሰረቱ ውልድ ስሞች ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ቅፅል</u> | <u>ስም</u> | | |
| ድርስ- | ድርስ-ኧት | ድርሰት | 7 |
| ቅብጥ- | ቅብጥ-ኧት | ቅብጠት | |
| ክስር- | ክስር-ኧት | ክስረት | |
| ፍጥር- | ፍጥር-ኧት | ፍጥረት | |
| ውፍር- | ውፍር-ኧት | ውፍረት | |
| ውርድ- | ውርድ-ኧት | ውርደት | |
| ግድፍ- | ግድፍ-ኧት | ግድፈት | |

የእነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ዕስር እምዶች ክፍል በርግጥ ቅፅል መሆኑ አጠራጣሪ ነው፡፡ ክፍላቸው ምናልባትም ስም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነበት ምክንያት ስምና ቅፅል ተመሳሳይ የሆነ የአምድ አመሰራረት ስርዓት ሊከተሉ ስለሚችሉ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ *ቅርፅ* የሚለውን ስምና *ብልጥ* የሚለውን ቅፅል ብናነፃፅር፣ የአምድ አመሰራረታቸው ስርዓት አንድ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ሁለቱም አምዶች የተመሰረቱት ከሶስት ተናባቢና /እ/ ከሚለው አናባቢ ነው፡፡ በሁለቱም አምዶች ውስጥ አናባቢው ድምፅ የሚገኝበት ቦታ ከመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ ቀጥሎ ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ማለት ነው፡፡

/ተ-ተ-ተ/ ⟶ [ተእተተ]

ተ= ተናባቢ

ይህን ስርዓት ተከትሉ እንደ *ብልጥና ቅርፅ* ያሉ ነፃ አምዶችን ባንድ በኩል፣ እንደ *ውፍር-* እና *ግድፍ-* ያሉ ዕስር አምዶችን በሌላ በኩል መመስረት ስለሚቻል፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ የዕስር አምዶችን የቃል ክፍል በውል

ለመለየት አስቸጋሪ ነው። መለየት የማያስቸግረው እንደ ውፍረትና ግድፈት ያሉትን ውልድ ቃላት ክፍል ነው።

ከላይ የሚታየው የተናባቢና የአናባቢ አቀነጃጀት እንደ ልብስ፣ ፍርድ፣ ምርት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን አፈጣጠር የሚያካትት ስለሆነ፣ የስምና የቅፅል የጋራ ስርዓት ነው፣ ለማለት ይቻላል። በዚህ አመለካከት መሰረት ከላይ በተራ ቁጥር (1) ያስቀመጥነውን ስርዓት እንደሚከተለው አድርገን ማሻሻል ይኖርብናል።

ስርዓት 2፣

| | | |
|---|---|---|
| [{ስም፣ ቅፅል}+[{–ነት፣–ኧት}] | ⟶ | [ስም] የረቂቅ |

ስርዓቱ ከስም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንንኧት/ ወይም /–ኧት/ የሚለውን ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር አዳዲስ የረቂቅ ስሞችን መፍጠር ይቻላል፣ የሚል ነው። ለምሳሌ፣ ይህን ህግ በመከተል እንደ ንድፈት፣ ንቅፈት፣ ንፍቀት፣ ፅንፈት፣ ንጥፈት፣ ግልፀት፣ ብግነት፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ስሞችን በመፍጠር ለአዳዲስ ስንፀ-ሀሳብ መግለጫ ማዋል ይቻላል። ስርዓቱ እንደ ቅብጠት ያለ ቃላትን ውስጣዊ አቀነጃጀት ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን፣ እንደ ንፍቀት ያሉና ገና በጥቅም ላይ ያልዋሉ ዕንስ-ቃላትንም አፈጣጠር ያሳያል።

የረቂቅ ስሞች ረቂቅ ባህሪን ስለሚያመለክቱ የብዛት ምልክት የላቸውም። በዚህም አካላዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚያመለክቱት ተቆጣሪ ስሞች ይለያሉ። ለምሳሌ፣ ልጅ ብሎ፣ ልጅ-ኦች ማለት ሲቻል፣ ብልጠት ብሎ ብልጠት-ኦች ማለት ግን አይቻልም። ብልጠት ሊቆጠር የሚችል የቁሳዊ ነገር ስም አይደለምና።

ከረቂቅ ስሞች በተጨማሪ ሌሎች ስሞችንም ከነባር ስሞችና ቅፅሎች ላይ መመስረት ይቻላል። ስሞቹ የሚመሰረቱት ከአንዳንድ የወል ስሞችና የባህሪ ቅፅሎች ላይ /-ኦ/ የሚል ምዕላድ እንደሚከተለው በመጨመር ነው።

| ስም | ውልድ | | 8 |
|---|---|---|---|
| ውሻ | ውሽ-ኦ | ውሾ | |
| ሌባ | ሌብ-ኦ | ሌቦ | |
| ንፉጥ | ንፍጥ-ኦ | ንፉጦ | |
| ቅፅል | ስም | | |
| ቂል | ቂል-ኦ | ቂሎ | |
| ሞኝ | ምኝ-ኦ | ሞኞ | |
| ብልጥ | ብልጥ-ኦ | ብልጦ | |

የአፈጣጠራቸው ስርዓት የሚከተለውን ይመስላል።

ስርዓት 3፣

| |
|---|
| [[[{ስም፣ ቅፅል}] + [-እ]] ⟶ [ ስም] መጥሪያ |

ስርዓቱ ከቅፅል ወይም ከስም ላይ /-እ/ ሲጨመር፡ የመጥሪያ ስም እንደሚፈጠር ያመለክታል፡፡

እንደነዚህ አይነቶቹ የባህሪ ስሞች ናቸው፡፡ አንድ ሰው ሌባ ከሆነ፣ ይህን ባህሪውን ለመግለፅ በመደበኛ ስሙ ሳይሆን፣ በባህሪው ሌቦ ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ ካሳ፣ አበበ፣ አስቴር፣ ወዘተ፡ ብለን አንድን ሰው በተፀውዖ ስሙ እንደምንጠራው ሁሉ፣ እንደ ባህሪው አይነት ሌቦ፣ ውሾ፣ ወዘተ፡ እያልን በባህሪው ልንጠራው እንችላለን፡፡

እንደ ሌቦ ያሉ ስሞችን ከሌሎች ስሞች ለየት የሚያደርጋቸው ስዋስዋዊ ሳይሆን፣ ርባታዊ ባህሪያቸው ነው፡፡ ይህም እንደ ሌሎች ስሞች የቁጥር ምዕላድ የሆነውን /-አችች/ን ለማስከተል አለመቻላቸው ነው፡፡ እንደነዚህ አይነት ስሞች ብዛትን (ጥቂትነትን) የሚያሳዩት /እንንኧ-/ የሚለውን እጉዋዳኝ ምዕላድ በማስቀደም ነው፡፡ ስለዚህም፡ እነ-ሌቦ እንጅ፣ ሌቦች ብሎ መጥራት አይቻልም፡፡ ሌቦች ብሎ መሳደብ ግን ይቻላል፡፡ /እንንኧ-/ የሚለው ምዕላድም ከተፀውዖ፣ ማለትም ከመደበኛ የመጥሪያ ስሞችና ከዚህ በፊት ባየነው ክፍል እንደተገለፀው፣ ከጠቋዋሚ መስተዓምሮችና ተውላጠ ስሞች ጋር የሚሄድ ምዕላድ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ካሳ ብሎ፣ እነ-ካሳ እንጅ፣ ካሳ-እች አይባልም፡፡ እንደዚሁም ይህ ብሎ እነ-ይህ (እነዚህ) እንጅ ይህ-እች አይባልም፡፡ እንደ ሌቦ ያሉ ስሞችም ልክ እንደ ካሳ አይነት ስሞች፡ /እንንኧ-/ የሚለውን ምዕላድ መውሰዳቸው፡ ክፍላቸው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከተፀውዖ ስሞች ጋር ነው፡ ለማለት ያስችላል፡፡

በስዋስዋዊ ባህሪያቸው፣ የመጥሪያ ስሞች ከወል ስሞች የተለዩ አይደሉም፡፡ እንደ ማንኛውም የወል ስም በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ወይም ተሳቢ ሆነው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ መጣ 9
(ለ) ሌቦ መጣ

ማለት እንደሚቻል ሁሉ፣

(መ) ካሳን አየሁት
(ለ) ሌቦን አየሁት

ማለት ይቻላል፡፡

እስካሁን የተመለከትነው፣ ስሞች ከቅፅል ወይም ከሌሎች ስሞች እንዴት እንደሚመሰረቱና ቅርፃዊ ባህሪያቸውም ምን እንደሚመስል ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስሞች ከግሳዊ ስሮች ወይም እምዶች ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ እናያለን፡፡ ወደ ዝርዝሩ ከመሄዳችን በፊት ግን ስር ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በአማርኛ፣ የማናቸውም ግስ እንደዚሁም

የተወሰኑ ቅፅሎችና ስሞች መሰረት፣ ተናባቢ ድምፆች ናቸው፡፡ የተናባቢዎቹ ቁጥር ከአንድ እስከ ስድስት እንደሚደርስ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡

እያንዳንዱ ተናባቢ ድምፅ እግር ይባላል፡፡ ተናባቢዎቹ አንድ ላይ ሆነው የሚፈጥሩት ቅንጅት ስር ይባላል፡፡ ይህ ስር እንደ ተናባቢዎቹ ቁጥር ባለ ሁለት፣ ባለሶስት፣ ወዘተ፣ እግር እየተባለ ይለያል፡፡ ስሩ ብቻውን አጠቃላይ የሆነ ቅርፅና ትርጉም አለው፡፡ ስለዚህም ምዕላድ ነው፡፡ ለምሳሌ /ብ - ል- ጥ-/ የሚለውን ስር ብንወስድ፣ ከመብለጥ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሆነ ትርጉም እንዳለው እንረዳለን፡፡ ቅርፁም እንደዚሁ ከተናባቢዎች ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ አሻሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚሁ ስር ላይ ቅፅልን፣ ግስን ወይም ስምን መፍጠር ስለሚቻል ነው፡፡ አሻሚነቱን ለማገድ፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ስናደርግ፣ የሚፈጠረው ቅርፅ <u>አምድ</u> ይባላል፡፡ አምዱ የግስ፣ የቅፅል ወይም የስም ሊሆን ይችላል፡፡ በአቋዋሙም ነፃ ወይም ዕስር ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አምድ ላይ፣ ልዩ ልዩ ቅጣዮችን በመጨመር የተለያዩ ቃላትን መመስረት ይቻላል፡፡ የተመሰረቱትን ቃላት ክፍልም ማወቅ ይቻላል፡፡ የስሩን ክፍል ማወቅ ግን አይቻልም፡፡ የሁሉም እናት ስለሆነ ሁሉ-ገብ ነው፡፡ ይህ የአማርኛ ብቻ ሳይሆን የሴም ቋዋንቋዋዎች አጠቃላይ ባህሪ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው፣ ውልድ ስሞች ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ከስሩ የሚፈጠሩት፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ አናባቢዎችን በመጨመር ሲሆን፣ ከአምዱ ላይ የሚፈጠሩት ቅጣዮችን፣ ማለትም መስራች ምዕላዶችን፣ በማስከተል፣ በማስቀደም ወይም የየስሩን ተናባቢ በመድገም ነው፡፡ ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ከግስ ስር የሚመሰረቱት የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

| <u>ስር</u> | <u>ስም</u> | 10 |
|---|---|---|
| /ል- ብ- ስ/ | [ልእብስ] | ልብስ |
| /ጥ- ቅ- ም/ | [ጥእቅእም] | ጥቅም |
| /ም- ር- ት/ | [ምእርት] | ምርት |
| /ው- ር- ስ/ | [ውእርስ] | ውርስ |

እነዚህ አይነት ስሞች በግሱ ስር ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች፣ ባንዱ ወይም በሁሉቱም ላይ /እ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ በመጨመር የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ሁኔታው /እ/ የሚለውን ድምፅ፣ ስም መስራች ምዕላድ ነው፣ ሊያሰኝ የሚችል ይመስላል፡፡ በርግጥ ይህን ማለት ግን አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ድምፅ በስሩ ውስጥ የሚታዩትን ሶስቱን ተናባቢ ድምፆች ከተራ ድምፅነት ወደ ቀለምነት የመለወጥ ስነ-ድምፅ ልሳናዊ የሆነ ተግባር ስላለው ነው፡፡ ይህን ተግባር በሚፈፅምበት ጊዜ የሚፈጠረው ቅርፅ እንዳጋጣሚ ስም ሲሆን ችሎአል፡፡ ሌላም ሊሆን ይችል ነበር፣ ለምሳሌ ቅፅል፡፡ ይህን ወደ ሁዋላ በቦታው

እናየዋለን፡፡ ከዚህ ላይ ግን ከግስ ስር ላይ [እ]ን በመጨመር የሚፈጠር ስም፣ አፈጣጠሩ ስነ- ምዕላዳዊ ነው ከማለት ይልቅ፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፤ ማለቱ የሚበጅ ላይሆን አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ከቁዋንቁዋው የቀለም አወቃቀር ስርዓት አንፃር ስናይ፣ ለቀለሙ መፈጠር የአናባቢው /እ/ መግባት የግድ ነው፡፡ አናባቢው /እ/ ባይሆን ኖሮ፤ ስርዓቱ ስነ-ምዕላዳዊ ይሆን ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ ንጉስ [ንእግኡስ] የሚለውን ስም ብንመለከት፣ /ን-ግ-ስ/ ከሚል ስር ላይ /እ/ን እና /ኡ/ን በተናባቢዎቹ መካከል በማስገባት የተፈጠረ ቃል መሆኑን እንረዳለን፡፡ /እ/ የገባው በቀለማዊ ስርዓት መስረት ነው፡፡ በስነ-ድምፁ ክፍል እንዳየነው፣ በቃል መነሻ ላይ ቁዋንቁዋው የተናባቢ ክትትሎሽን አይፈቅድም፡፡ ተናባቢዎች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ፤ ክትትሎሹን ለመስበር [እ] በመካከላቸው ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚገባው /እ/ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፡፡ የተናባቢ ክትትሎሽ በሚፈቀድበት አውድ ላይ የሚገባ /እ/ ወይም ሌላ አናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት [ንእግኡስ] በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው [እ] ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሲሆን፣ /-ኡ-/ የሚለው አናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር /-ኡ-/ ቅፅል መስራች ምዕላድ ነው፡፡ ምክንያቱም አገባቡ የተናባቢ ክትትሎሽን ለማገድ ላይሆን፤ በተናባቢ ብቻ ከተመሰረተው ስር ውስጥ ገብቶ ቃል ለመፍጠር ስለሆነ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ቁዋንቁዋው በቃል መሀል እና መጨረሻ ላይ የሁለት ተናባቢ ክትትሎሽን ይፈቅዳል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም እንደ ውርስ ያሉ ስሞችን ከግሱ ስር ከመመስረት ይልቅ፣ ለምን ከራሱ ከግሱ መመስረት አይቻልም? የሚል ነው፡፡ ይህም ውርስ የሚለውን ስም ለምን ወረሰ ከሚለው ግስ ላይ በቀጥታ መመስረት አይቻልም? እንደ ማለት ነው፡፡ ርግጥ፤ ይህን ማለት ይቻላል፡፡ ግን ሂደቱ ብዙና ውስብስብ ነው፡፡ እስቲ እንመልከተው፡፡

ወረሰ የሚለው ግስ ድምፃዊ ቅንጅት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

/ው - ኧ - ርር - ኧ - ስ -ኧ/ 11

በዚህ ቅንጅት ውስጥ ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች አሉ፡፡ ውርስ በሚለው ስም ውስጥ ግን ከላይ እንዳየነው፣ አንድ የ/እ/ ድምፅ ብቻ ይታያል፡፡ እንግዲህ ውርስ የሚለው፤ ወረሰ ከሚለው ግስ ላይ ተመሰረተ ብንል፣ አንደኛ፣ ወረሰ ውስጥ ያሉት ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች ወደ አንድ የ/እ/ ድምፅ ተለውጠዋል፤ ወይም ከናካቴው ጠፍተዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ለውጥ መግለፁ ራሱ አንድ ስራ ነው፡፡ አስቸጋሪም ነው፡፡ ምክንያቱም ለለውጡ ጥሩ መንስዔ መስጠት የሚቻል አይመስልም፡፡ ሁለተኛ፣ ወረሰ የሚለው ግስ ስም የሚሆነው /ኧ/ የሚለው ድምፅ ወደ /እ/ ሲለወጥ ነው ካልን፣ /እ/ ስም መስራች ምዕላድ እንጅ፤ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ተናባቢዎቹን ድምፆች ወደ ቀለም የሚለውጥ ድምፅ አይደለም፤ ማለት ነው፡፡ በሌሎች ቃላት ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን /እ/ ቀለም መስራች መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ብልህ /ብእልህ/ በሚለው ቅፅል ውስጥ /እ/

አለ፡፡ ይህ /እ/ ግን ቅፅል መለራች አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቅፅሉ የሚመሰረትበት "በለኸ" የሚል ግስ በቋንቋው ውስጥ የለም፡፡ ይህም አናባቢው /እ/ የገባው በቀለም መሰራችነት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ፣ /ውእርስ/ በሚለው ስም ውስጥ ያለው /እ/ም እንደዚሁ ቀለም መሰራች ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን ካልን ደግሞ፣ ቃሉ ወረሰ ከሚለው ግስ /ኧ/ን በ/እ/ ለውጦ የመጣ ነው፣ የሚለው አመለካከት ትክክል አይሆንም፡፡ አቋራጩና ትክክለኛ የሚመስለው መንገድ፣ /ውእርስ/ የሚለው ስም /ው - ር - ስ/ ከሚለው ስር ላይ በቀጥታ ተመሰረተ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ከተስማማን፣ እንደ ውርስ ያሉ ስሞች የሚፈጠሩበትን አጠቃላይ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ስርዓት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 4፡

/ተ - ተ - ተ/ ⟶ [ተእተተ]

ከምሳሌው እንደሚታየው፣ ከዚህ ስርዓት እንደ ውርስ ያሉ ነፃ እምዶችን መፍጠር ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ስርዓት እንደ [ቅእልም-] ያሉ ዕስር እምዶችንም መፍጠር ይችላል፡፡ ከነሱም ላይ እንደ /-እኸ/ እና እንደ /-ንንእ/ ያሉ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር፣ የሚከተሉትን አይነት ስሞች መፍጠር ይቻላል፡፡

| ስር | ስም | | 12 |
|---|---|---|---|
| ቅልም- | ቅልም-እኸ | ቅልሞሽ | |
| ስርቅ- | ስርቅ-እኸ | ስርቆሽ | |
| ግርድ- | ግርድ-እኸ | ግርዶሽ | |
| ጥብቅ | ጥብቅ-ንንእ | ጥብቅና | |
| ድርቅ | ድርቅ-ንንእ | ድርቅና | |
| ግብር- | ግብር-ንንእ | ግብርና | |
| ትህት- | ትህት-ንንእ | ትህትና | |

/-እኸ/ የሚለው ምዕላድ የሚጨመረው፣ እንደነዚህ ባሉ እስር እምዶች ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በነፃ እምዶች ላይም ሊቀጠል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ቅብብል ብሎ ቅብብል-እኸ፣ ድብብቅ ብሎ ድብብቅ-እኸ፣ ድግግም ብሎ ድግግም-እኸ፣ ወዘተ፣ ማለት ይቻላል፡፡ እንደነዚህ አይነት ስሞች አንዳንድ ጊዜ የአንድን ነገር ተደጋጋሚ ሂደት ሲያመለክቱ፣ ሌላ ጊዜ ውጤቱን ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) ልጆቹ ቅብብሎሽ ይጫወታሉ 13

ብንል፣ ቅብብሎሽ የሚለው ስም የሚያመለክተው የአንድን ነገር የመቀባበል ረዥም ሂደት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣

(ለ) ካሳ ጥሎሽ ጥሉ (ለጥቶ) ሚስት አገባ

ብንል፣ ጥሎሽ የሚለው ቃል የሚገልፀው፣ ለሙሽራ የሚሰጠውን ስጦታ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በዚህ ትርጉሙም ቢሆን፣ ለሙሽራ ስጦታ ሲሰጥ ጣል ጣል የማድረግን ተደጋጋሚ ድርጊት ሊያሳይ ይችላል፡፡

/-ንንእ/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት የሚፈጠሩት፣ እንደ ግብርና ያሉት፣ አንድ ሰው የሚሰራበትን ወይም የሚኖርበትን ሁኔታ ወይም ሙያ ስለሚያመለክቱ፣ የሙያ ወይም የሁኔታ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡

ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንደተዘረዘሩት ያሉ ናቸው፡፡

| እምድ | ስም | | 14 |
|---|---|---|---|
| ሰብር- | ሰብር-አት | ስብራት | |
| ሽልም- | ሽልም-አት | ሽልማት | |
| ሰቅል- | ሰቅል-አት | ሰቅላት | |
| ንቅስ- | ንቅስ-አት | ንቅሳት | |
| ዕርም- | ዕርም-አት | ዕርማት | |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ ስሞቹ የተፈጠሩት ከዕስር ምዕላዶቹ ላይ /-አት/ የሚለውን መስራች ምዕላድ በመቀጠል ነው፡፡ በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ስሞች አንድ ነገር ከተደረገ በሁዋላ የሚገኘውን ውጤት ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ዕርማት የሚለው ስም የሚያመለክተው አንድ ነገር ከታረመ በሁዋላ፣ የሚገኘውን ውጤት ነው፡፡ የማረሙን ሂደት የሚያመለክተው ቃል ዕረማ ሲሆን፣ የዚህ ሂደት ውጤት ደግሞ ዕርማት ይባላል[2]፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር (4) በተመለከተው ስርዓት መሰረት ([ተእተ(ተ)-]) በሚወጡ ሌሎች ዕስር እምዶች ላይ /-አት/ ወይም /-አትእ/ የሚል ሌላ ምዕላድ በመጨመር እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል፡፡

---

[2] ይሁን እንጅ፣ እርማት የሚለው ራሱ እንደ ሂደት ስም ስለሚያገለግል ዐረማ የሚለውን ቃል አግዶታል፡፡ ዐረማ በሂደት ስምነት የሚታወቀው ዐረም ከማረም ጋር በተያያዘ ቅርፁ ነው፡፡ ርግጥ፣ ሁለቱም የማይፈለግ ነገርን ከሚፈለገው እየለዩ የማስወገድን ተግባር ያለመለከታሉ፡፡

| አምድ | ስም | 15 |
|---|---|---|
| ፍጅ | ፍጅ-አትአ | ፍጆታ |
| ችል- | ችል-አትአ | ችሎታ |
| ስም | ስም-አትአ | ሰሞታ |
| ብስ- | ብስ-አት | ብሶት |
| ቅንጥ- | ቅንጥ-አት | ቅንጠት |
| ስርቅ- | ስርቅ-አት | ስርቆት |

እንደነዚህ ያሉ ስሞችም የሚያመለክቱት ውጤትን ይመስላል፡፡ ስምሳሌ፣ አንድ ሰው የሚፈጀው ነገር ፍጆታው ሲሆን፣ የሚችለው ነገርም እንደዚሁ ችሎታው ነው፡፡ ሁኔታው የተለያየ ቅርፅ ያላቸው የውጤት ስሞች እንዳሉ ያሳያል፡፡

እስካሁን ያየናቸውን የውልድ ሰሞች የአመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው አድርጎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ሰርዓት 5፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [ ተአተ-(ተ)-(አ)ተ] + [ {-ኧት፣-አሽ፣-ኢት፣-አ፣-አት፣-አትአ፣-አንንአ} ] | | ⟶ | [ስም] |
| አምድ | ቅጣይ | | ውጤት |

በአምዱ ውስጥ፣ በቅንፍ የተመለከቱት ተናባቢና አናባቢ ድምፆች ሲኖሩም፣ ላይኖሩም ይችላሉ፡፡ የተናባቢዎቹ መኖር ወይም አለመኖር፣ የሁለተኛውን (የተከታዩን) አናባቢ ድምፅ መኖር ወይም አለመኖር ይወሰናል፡፡ እነሱ ሲገኙ፣ እሱም ይገኛል፡፡

ከዚህ በላይ ተጠቃሎ የተቀመጠው አንዱ አይነት የስሞች አመሰራረት ስርዓት ሲሆን፣ ሌላው አይነት የሚከተሉት ስሞች የሚፈጠሩበት ነው፡፡

| | ስር | አምድ | ስም | 16 |
|---|---|---|---|---|
| (ሀ) | /ድ - ከ - ም/ | /ድ - ከአም/ | [ድእከአም] | ድካም |
| | /ጥ - ግ - ብ/ | /ጥ - ግአብ/ | [ጥእግአብ][3] | ጥጋብ |
| | /ድ - ግ - ፍ/ | /ድ - ግአፍ/ | [ድእግአፍ] | ድጋፍ |
| | /ዝ - ን - ብ/ | /ዝ - ንአብ/ | [ዝእንአብ] | ዝናብ |
| | ስር | አምድ | ስም | |
| (ለ) | /ቅ - ድድ-ስ/ | /ቅ - ድድአስ-/ | [ቅእድድአስ-ኤ] | ቅዳሴ |
| | /ግ - ስስ -ፅ/ | /ግ - ስስአፅ-/ | [ግእስስአፅ-ኤ] | ግሳፄ |
| | /ው - ድድ-ስ/ | /ው - ድድአስ-/ | [ውእድድአስ-ኤ] | ውዳሴ |
| | /ት - ክክ -ዝ/ | /ት- ክክአዝ-/ | [ትእክክአዜ-ኤ] | ትካዜ |

[3] አቀራረቡ ድምፀ ልሳናዊ ሂደትን አያመለክትም፡፡

በ(ሀ) ውስጥ የተዘረዘሩት ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /አ/ን በማስገባት የሚፈጠሩ ስሞች ናቸው፡፡ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /አ/ የተናባቢ ከትትሎሽ እንዳይፈጠር የገባ አናባቢ ነው፡፡ ተግባሩ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ስለሆነ፣ ስለሞቹ ምስረታ አስተዋፅዖ የሚያደርገው /አ/ ብቻ ነው፡፡

በ(ለ) ስር የሚታዩት፣ በ(ሀ) ስር እንዳሉት፣ /አ/ የሚለውን አናባቢ ከመድረሻው ተናባቢ በፊት በማስገባት፣ እምድ የሚፈጠሩና በየእምዱ መድረሻ ላይም /-ኤ/ የሚለውን ምዕላድ በመቀጠል የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /እ/ የተናባቢ ከትትሎሽ እንዳይኖር የገባ አናባቢ ነው፡፡ የስሞቹን የአመስራረት ስርዓት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 6፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተ(-ተ)አተ-] + [(-ኤ)]] | | ⟶ | [ተእተ-(ተ)አተ-(ኤ)] |
| እምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች የሚያመለክቱት የአንድን ተግባር ውጤት ነው፡፡ ለምሳሌ <u>ውዳሴ</u> የሚለው ስም የሚገልፀው፣ ተግባርን ወይም ሂደትን ሳይሆን፣ የሂደትን ውጤት ነው፡፡ የሂደቱ ስም ው<u>ደሳ</u> ሲሆን፣ የተግባሩ ስም <u>ማወደስ</u> ወይም በግዕዝ መልኩ <u>መወድስ</u> ነው፡፡

ከላይ ከቀረቡት የተለየ የአመስራረት ስርዓት ያላቸው የውጤት ስሞችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>እምድ</u> | <u>ስም</u> | 17 |
|---|---|---|
| ውጥ- | ውጥ-ኤት | ውጤት |
| ስል- | ስል-ኤት | ስሌት |
| ስም- | ስም-ኤት | ስሜት |
| ምር- | ምር-ኤት | ምሬት |
| ስክ- | ስክ-ኤት | ስኬት |
| ቅል- | ቅል-ኤት | ቅሌት |

እምዶቹ ዕስር ናቸው፡፡ የንግግር ክፍላቸውን በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከእነሱ ላይ /-ኤት/ የሚለውን ቅጣይ በመጨመር ስሞቹን መመስረት ይቻላል፡፡ የአመስራረት ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 7፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተተ-] + [-ኤት]] | | ⟶ | [ተእተተ-ኤት] |
| እምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ከሌሎች ዕስር አምዶች ላይ ተከታይ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

| አምድ | ስም | | 18 |
|---|---|---|---|
| ድርግ- | ድርግ-ኢት | ድርጊት | |
| ቅንጅ- | ቅንጅ-ኢት | ቅንጅት | |
| ግፍ- | ግፍ-ኢት | ግፊት | |
| ዕልቅ- | ዕልቅ-ኢት | ዕልቂት | |
| ድርጅ- | ድርጅ-ኢት | ድርጅት | |
| ስርጭ- | ስርጭ-ኢት | ስርጭት | |
| ትንብ- | ትንብ-ኢት | ትንቢት | |

እነዚህ የውጤት ስሞች ይመስላሉ፡፡ ምናልባትም፣ እንደ ስርጭት ያሉት የሂደት ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሂደት ስሞች አንድ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊትን እንደሚገልፁ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ መዋቅራዊ ባህሪያቸው [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድዳዊ አውድ ውስጥ ለመግባት መቻል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) መድሀኒቱ በስርጭት ላይ ነው 19
(ለ) ወታደሮቹ በውጊያ ላይ ናቸው
(መ) *ወታደሮቹ በትንቢት ላይ ናቸው

ስርጭትና ዕልቂት [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድድ ውስጥ ገብተው ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ሊመሰርቱ ችለዋል፡፡ ትንቢት የሚለው ስም ግን በዚሁ ቦታ ገብቶ የፈጠረው አረፍተ ነገር ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህም በመነሳት ስርጭት የሂደት፣ ዕልቂት የውጤት ስም ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ የሁለቱ ስሞች ስነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ አገባባዊ ባህሪያቸው ለየቅል መሆኑን ከምሳሌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ ጊዜ የሂደትና የውጤት ስሞችን በአገባባቸውም ቢሆን ለመለየት ያስቸግራል፡፡ ይህን ዝቅ ብለን እንመለከታለን፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ስሞች አመሰራረት ግን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 8፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተ-(እ)ተ-ተ) ] - + [-ኢት]] | | ⟶ | [ተእተ-(እ)ተ-(ተ)-ኢት] |
| አምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ደግሞ እንመልከት፡፡

| አምድ | ስም | | 20 |
|---|---|---|---|
| ግፍ- | ግፍ-ኢይአ | ግፊያ | |
| ግብዝ- | [ግአብዝ--ኢይአ] | [ግአብዥአ] | ግብዣ |
| ዝርፍ- | ዝርፍ-ኢይአ | ዝርፊያ | |
| ሽም- | ሽም-ኢይአ | ሽሚያ | |
| ቅድም- | ቅድም-ኢይአ | ቅድሚያ | |
| ግጥም- | ግጥም-ኢይአ | ግጥሚያ | |
| ፍልም- | ፍልም--ኢይአ | ፍልሚያ | |
| ድርስ- | [ድአርስ-ኢይአ | [ድአርሽአ] | ድርሻ |

እነዚህ የተመሰረቱበት አምድ ከላይ በተራ ቁጥር(8) የሚታየው አይነት ሲሆን፣ መስራቹ ምዕላድ /-ኢይአ/ ነው፡፡ ስርዓቱም የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 9፣

[[(ተአተ-ተ) - + [--ኢይአ]] ⟶ [ተአተ--ተ)-ኢይአ]
አምድ ቅጣይ የሂደት ስም

በዚህ ስርዓት መስረት የሚፈጠሩ ስሞች በአብዛኛው ሂደትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ውጤትንም ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ግብዣ የሚለውን ስም ብንወስድ፣ በአንድ ምክንያት የተዘጋጀ ድግስን፣ ማለትም ውጤትን፣ ወይም ድግሱን የመብላትን ሂደት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ትርጉሙ አሻሚ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድርሻ የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ አንድ ሰው አንድ ነገር ከሌሎች ጋር ተካፍሎ ሲጨርስ፣ የሚደርሰውን መጠን ስለሚያመለክት የውጤት ስም ነው፡፡

ሌሎች የማያሻሙ የውጤት ስሞችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| አምድ | ስም | 21 |
|---|---|---|
| ሽፍት- | ሽፍት-አ | ሽፍታ |
| ቁምጥ- | ቁምጥ-አ | ቁምጣ |
| ጭፍን- | ጭፍን-አ | ጭፍና |
| ጭፍር- | ጭፍር-አ | ጭፍራ |
| ብስን- | ብስን-አ | ብስና |

የእነዚህ የአመሰራረት ስርዓት የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 10፤

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተአተተ-] + [-አ] | ⟶ | [ተአተተ-አ] |
| አምድ ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ስርዓቱ በየዕስር አምዱ ላይ /-አ/ የሚሰውን መሰራች ምዕላድ መቀጠል እንደሰብን ያሳያል፡፡

አሁን ደግሞ ወደ ሌሎች የውጤት ስሞች አመሰራረት እንሂድና የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

| ስር | ስም | 22 |
|---|---|---|
| /ስ - ር - ግ/ | [ሰእርግ] | ሰርግ |
| /ም - ል - ስ/ | [ምእልሰ] | መልስ |
| /ሽ - ፍ - ጥ/ | [ሽእፍጥ] | ሽፍጥ |
| /ብ - ል - ግ/ | [ብእልግ] | በልግ |
| /ስ - ል - ፍ / | [ሰእልፍ] | ሰልፍ |
| /ጥ - ር - ብ/ | [ጥእርብ] | ጠርብ |

የነዚህና የመሳሰሉት ስርዓት የሚከተሰው ነው፡፡

ስርዓት 11፤

| | | |
|---|---|---|
| [ተ-ተ-ተ] | ⟶ | [ተእተተ] |
| ስር | | የውጤት ስም |

ስርዓቱ ከየስሩ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ /እ/ የሚሰውን እናባቢ በማስገባት የውጤት ስሞችን መፍጠር እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ በዚህ ሰርዓት ከሚመሰረቱትም ብዙዎቹ ነፃ አምዶች ናቸው፡፡ በነሱ እና በጥቂት ሌሎች አምዶች ላይ /-እኘኘአ/ የሚል ምዕሳድ በመጨመር እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መፍጠር ይቻላል፡፡

| ሰም | ስም | 23 |
|---|---|---|
| ግንብ | ግንብ-እኘኘአ | ግንበኛ |
| ሰልፍ | ሰልፍ-እኘኘአ | ሰልፈኛ |
| ፈረስ | ፈረሰ-እኘኘአ | ፈረሰኛ |
| ጥበብ | ጥበበ-እኘኘአ | ጥበበኛ |
| ሰፈር | ሰፈረ-እኘኘአ | ሰፈረኛ |

እንደ <u>ስልፍ</u> ያሉት የውጤት ስሞች ሲሆኑ፣ ከእነሱ ላይ የሚመሰረቱት እንደ <u>ሰልፈኛ</u> ያሉት የውጤቱን ባለቤት ወይም ተሳታፊ የሚያመለክቱ ስሞች ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት የሙያተኛ ስሞች ሲባሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ግንበኛ በግንብ ስራ ላይ የተሰማራ ሙያተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ እንደ <u>ሰፈረኛ</u> (ሰፈርተኛ) ያሉት በተለያየ ሰፈር የሚኖርን ሰው ስለሚያመለክቱ፣ የአካባቢ ነዋሪዎች ስሞች ሲባሉ ይችላሉ፡፡ ስርዓታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 12፣

| | |
|---|---|
| [[ስም] + [-ኧኝ/ኛ/እኛ]] ቅጣይ → | [ስም] የሙያ ስም |

ከፍ ሲል ካየናቸው በተጨማሪ፣ ያለምንም ቅጣይ ምዕላድ በየስሩ ውስጥ በሚታዩት ክፍት ቦታዎች ላይ /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በመጨመር ብቻ የሚፈጠሩ ሌሎች የውጤት ስሞች አሉ፡፡ እነሱም የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

| <u>ስር</u> | <u>ስም</u> | | |
|---|---|---|---|
| | | | 24 |
| /ቅ - ል - ም/ | [ቅኧልኧም] | ቀለም | |
| /ቅ - ር - ጥ/ | [ቅኧርኧጥ] | ቀረጥ | |
| /ቅ - ልል -ብ/ | [ቅኧልልኧብ] | ቀለብ | |
| /ም -ድ - ብ/ | [ምኧድኧብ] | መደብ | |
| /ን - ግ - ር/ | [ንኧግኧር] | ነገር | |
| /ዝ - ፍ - ን/ | [ዝኧፍኧን] | ዘፈን | |
| /ግ - ድ - ብ/ | [ግኧድኧብ] | ገደብ | |
| /ስ - ብ - ብ/ | [ስኧብኧብ] | ሰበብ | |

የነዚህም ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 13፣

| | |
|---|---|
| [ተ-ተ(ተ)-ተ] ስር → | [ተኧተ-(ተ) ኧተ] የውጤት ስም |

እንደ /-ኧ-/ ያሉ በየስሩ ውስጥ እየገቡ ቃል የሚመሰርቱ አናባቢዎች *ስረ-ገብ* መስራች ምዕላድ ሲባሉ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጅ፣ /-ኧ-/ን በማስገባት የሚፈጠሩ ዕስር አምዶችም አሉ፡፡ ከእነሱ ላይ ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር የሚፈጠሩት ግን ነፃ ናቸው፡፡ የሚከተሉት የእነሱ ምሳሌ ናቸው፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 25 |
|---|---|---|---|
| /ስ - ብ - ር/ | /ሰእበእር-/ | /ሰእበእር-አ/ | ሰበራ |
| /ፍ - ት - ን/ | /ፈእተእን-/ | /ፈእተእን-አ/ | ፈተና |
| /ዝ - ር - ፍ/ | /ዘእረእፍ-/ | /ዘእረእፍ-አ/ | ዘረፋ |
| /ድ - ግ - ፍ/ | /ደእገእፍ-/ | /ደእገእፍ-አ/ | ደገፋ |
| /ቅ - ዝ - ፍ/ | /ቀእዘእፍ-/ | /ቀእዘእፍ-አ/ | ቀዘፋ |
| /ም - ክ - ት/ | /መእከእት-/ | /መእከእት-አ/ | መከታ |

ቅጣዩ ምዕላድ /-አ/ ሲሆን፣ በእሱ አማካኝነት የሚፈጠሩት የሂደት ወይም የውጤት ስሞች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ ሰበራ እና ቀዘፋ ያሉት የአንድን ድርጊት ሂደት ሲያመለክቱ፣ እንደ ደገፋ እና ፈተና ያሉት ውጤትን ሊያመለክቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሂደት ስሞች በ----ላይ በሚል መስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ መግባት ስለሚችሉ፣ ከሌሎች አይነት ስሞች በቀላሉ ይለያሉ፡፡ ስለዚህም፣

ካሳ (በ) እንጨት ሰበራ ላይ እንዳለ ተጠራ 26

ማለት ይቻላል፡፡ የቀላቱን ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 14፣

| | | |
|---|---|---|
| [[-ተእተእተ-] [+-አ]] | ⟶ | [ተእተእተ-አ] |
| አምድ ቅጣይ | | የሂደት ስም |

ከስር አምድ ላይ የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞችን ደግሞ እንመልከት፣

| ስር | አምድ | ስም | 27 |
|---|---|---|---|
| /ስ-ብ-ክ/ | /ሰእብእክ-/ | /ሰእብእክ-እ/ | ሰባኪ |
| /ጥ-ር-ግ/ | /ጥእርእግ-/ | /ጥእርእግ-እ/ | ጠራጊ |
| /ው-ል-ድ/ | /ውእልእድ-/ | /ውእልእድ-እ/ | ወላጅ |
| /ት-ርር-ት/ | /ትእርርእት-/ | /ትእርርእት-እ/ | ተራች |
| /ፍ-ር-ድ/ | /ፍእርእድ-/ | /ፍእርእድ-እ/ | ፈራጅ |

እንደነዚህ ያሉት አድራጊ ስሞች ይባላሉ፡፡ አንድን ተግባር የሚፈፅምን አካል ወይም ሀይል ያመለክታሉ፡፡ የሚመሰረቱትም ከዕስሩ አምድ ላይ /-እ/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው፡፡ አምዱ በየስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ እና /-አ-/ን እንደ ቅደም-ተከተላቸው በማስገባት ይፈጠራል፡፡ በስነ-ድምፅ ክፍል እንዳየነው፣ /-እ/ የላዩኛ አናባቢ ስለሆነች፣ ቀድሞአት የሚገባውን ተናባቢ ወደ (ድ)ላንቃዊነት እንደምትለውጠው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የስሞቹን አፈጣጠር እንደሚከተሰው ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 15፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተ-ኽ-(ተ)ተ-አ-ተ-] [+ -ኢ] ] | ⟶ | [ ተ-ኽ-(ተ)ተ-ኣ-ተ-ኢ] |
| አምድ ቅጣይ | | የአድራጊ ስም |

ከዚህ ስርዓት ጋር ተቀራራቢ በሆነ መንገድ የሚከተሉትን አይነት ስሞች መፍጠር ይቻላል፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 28 |
|---|---|---|---|
| /ጥ-ርር-ግ/ | [ጥእርርኣግ-] | [ጥእርርኣግ-ኢ] | ጥራጊ |
| /ው-ድድ-ቅ/ | [ውእድድኣቅ-] | [ውእድድኣቅ-ኢ] | ውዳቂ |
| /ል-ቅቅ-ም/ | [ልእቅቅኣም-] | [ልእቅቅኣም-ኢ] | ልቃሚ |
| /ፍ-ልል-ጥ/ | [ፍእልልኣጥ-] | [ፍእልልኣጥ-ኢ] | ፍላጭ |

እንደነዚህ ያሉት ስሞች፣ አንድ ድርጊት ሲፈፀም ተርፎ ወይም ወድቆ የሚቀርን ነገር የሚያመስክቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም የቅሪት ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ስምሳሌ ጥራጊ የሚለው ስም ምርት ከተነሳ በሁዋላ አውድማ ተጠርጎ የሚገኝን ቀሪ ወይም ትርፍ እህል የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ በእንዳንድ አካባቢ ግርድ ይባላል፡፡ "ምርትና ግርዱ ይሰያል" የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

የዚህ አይነት ስሞች በትርጉማቸው ተደራጊ ናቸው፡፡ ይህን ለማመልከት ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን ያጠብቃሉ፡፡ ለምሳሌ ጠራጊን (/ጥኽርኣግ-ኢ/) እና ጥራጊን ([ጥእርርኣግኢ]) ብናነፃፅር፣ ጥራጊ ውስጥ የሚገኘው /ር/ ጥብቅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሌሎች ተደራጊ ስሞች ተደራጊነትን የሚያሳዩት /ተ-/ የሚል ምዕላድ በአድረጊው ስም መነሻ ላይ በማስገባት ነው፡፡ ይህም ጠራጊ ብሰን፣ ተ-ጠራጊ እንደምንለው ነው፡፡ ሁለቱን ተደራጊ ስሞች ስመለየት፣ እንደ ጥራጊ ያሉትን የድራጊ ስሞች ልንላቸው እንችላለን፡፡ ያፈጣጠር ስርዓታቸው እንደሚከተሰው ነው፡፡

ስርዓት 16፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተ-ተተኣተ][ +-ኢ]] | ⟶ | [ ተእተተኣተ-ኢ] |
| አምድ ቅ | | የድራጊ ስም |

እስካሁን የየናቸው ስሞች እንድም ከግሱ ስር ወይም ከአምዱ መድረሻና መካከል ላይ የተለያዩ መስራች ምዕላዶችን በመቀጠል የሚፈጠሩ ሲሆኑ፣ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ የሚፈጠሩት ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞች ናቸው፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 29 |
|---|---|---|---|
| /ስ-ድ-ብ/ | /-ስድኧብ/ | /ምኧ-ስድኧብ/ | መስደብ |
| /ስ-ብ-ር/ | /-ስብኧር/ | /ምኧ-ስብኧር/ | መስበር |
| /ፍ-ልል-ግ/ | /-ፍኧልልኧግ/ | /ምኧ-ፍኧልልኧግ/ | መፈለግ |
| /ጥ-ር-ግ/ | /-ጥርኧግ/ | /ምኧ-ጥርኧግ/ | መጥረግ |
| /ፍ-ል-ጥ/ | /-ፍልኧጥ/ | /ምኧ-ፍልኧጥ/ | መፍለጥ |

እንደነዚህ ያሉት ስሞች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አርዕስት በመባል ይታወቃሉ፡፡ ተግባራቸው ድርጊትን ማመልከት ስለሆነ የድርጊት ስሞች ልንላቸው እንችላለን፡፡ የሚፈጠሩት /ምኧ-/ የሚለውን ቅጥያ በየአምዱ መነሻ ላይ እንደሚከተለው በመቀጠል ነው፡፡

ስርዓት 17፣

| [[ምኧ-] +[-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ]] ⟶ | [ምኧ-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ] |
|---|---|
| ቅጣይ አምድ | የድርጊት ስም |

ከስርዓቱ እንደሚታየው፣ ከአምዱ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ ያለው አናባቢ /-ኧ-/ ሊገኝ ወይም ላይገኝ ይችላል፡፡ ይህን የሚወስነው የአምዱ ክፍል ነው፡፡ ቀደም ሲልም ሆነ፣ ባለፈው ንዑስ ክፍል እንደተጠቀሰው፣ የአማርኛ ግሶች የ(ሀ) እና የ(ለ) ተብለው በሁለት ክፍል ይመደባሉ፡፡ የ(ሀ) ክፍል የሚባሉት ቅድመ-መድረሻ እግራቸውን ሳያጠብቁ የሚመሰረቱና የሚረቡ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ በሚታየው የምስረታ ሂደት፣ አንድ አምድ የ(ለ) ክፍል ከሆነ፣ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ቀጥሎ /-ኧ-/ን ያስገባል፡፡ <u>በመስበርና</u> <u>በመፈለግ</u> መካከል የሚታየው የአመሰራረት ልዩነት ከዚህ የመነጨ ነው፡፡ <u>ሰበረ</u> የ(ሀ) ክፍል ግስ ሲሆን፣ <u>ፈለገ</u> የ(ለ) ክፍል ግስ ነው፣ ስለዚህም ቅድመ-መድረሻ እግሩን ያጠብቃል፡፡ ከመነሻ እግሩ ቀጥሎም /-ኧ-/ን ያስገባል፡፡

ከነዚህ አርዕስታዊ ስሞች ላይ /-ኢይእ/ የሚል ምዕላድ በመቀጠል ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል፡፡ ዝርዝሩን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

| | አርእስት | ስም | 30 |
|---|---|---|---|
| መጥረግ | /ምኧጥርኧግ/ | /ምኧጥርኧግ-ኢይእ/ | መጥረጊያ |
| መስበር | /ምኧስብኧር/ | /ምኧስብኧር-ኢይእ/ | መስበሪያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መግለጥ | /ምእግልእጥ/ | /ምእግልእጥ-ኢይአ/ | |
| | | [ምእግልእጭአ] | መግለጫ |
| መፍለጥ | /ምእፍልእጥ/ | /ምእፍልእጥ-ኢይአ/ | |
| | | [ምእፍልእጭአ] | መፍለጫ |

የዚህ አይነት ስሞች አንድ ነገር የሚፈፀምበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ መሳሪያ፣ ዘዴ፣ ወዘተ፡ ስለሚያመለክቱ፣ በጥቅሉ የማድረጊያ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ መሰረታቸውም ከፍ ሲል የተመለከትናቸው የድርጊት ስሞች ናቸው፡፡ የአፈጣጠራቸው ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 18፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ መ-ተ-ተእተ] +[ -ኢይአ]] | ⟶ | [መ-ተ-ተእተ-ኢይአ] |
| አምድ ቅጣይ | | የማድረጊያ ስም |

እስካሁን ያየናቸው ውልድ ስሞች ከግስ ስሮች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን በመጨመር ወይም ከአምዶች ላይ የተለያዩ መስራች ቅጣዮችን በማስቀደም ወይም በማስከተል የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ከነዚህ ለየት ያለ የአፈጣጠር ስርዓት ያላቸውን ስሞች እንመረምራለን፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 31 |
|---|---|---|---|
| /ስ-ብ-ር/ | /-ሰሰእብአብእር/ | /አ-ሰሰእብአብእር/ | አሰባበር |
| /ን-ግ-ር/ | /-ንንእግአግእር/ | /አ-ንንእግአግእር/ | አነጋገር |
| /ል-ብ-ስ/ | /-ልልእብአብእስ/ | /አ-ልልእብአብእስ/ | አለባበስ |
| /ል-ቅ-ስ/ | /-ልልእቅአቅእስ/ | /አ-ልልእቅአቅእስ/ | አለቃቀስ |
| /ው-ል-ድ/ | /-ውውእልአልእድ/ | /አ-ውውእልአልእድ/ | አወላለድ |

የነዚህ ስሞች አፈጣጠር፣ በየአምዱ ላይ ቀዳሚ ቅጣይ የሚጨምር ብቻ ሳይሆን፣ የየአምዱን የመነሻ እግር የሚያጠብቅ፣ ቅድመ-መድረሻውን የሚደጋግምና በተደጋጋሚዎቹ እግሮች መካከል /-አ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ የሚያስገባ ነው፡፡ መጀመሪያ የአምዱን አፈጣጠር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 19፡

/1 - 2 - 3/ ⟶ /-11እ2አ2እ3/

ከቀስቱ በፊት የሚታዩት ቁጥሮች የስሩን ሶስት ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በአንድ ቁጥር የተወከለው፣ ማለትም መነሻው፣ ተናባቢ ይጠብቃል፡፡ በሁለት ቁጥር የተወከለው፣ ቅድመ-መድረሻ ድምፅ ደግሞ ራሱን ይደግማል፡፡ ከዚያም በተደጋጋሚዎቹ ድምፆች መካከል /-አ-/ን፣ በሌሎቹ ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ን በማስገባት አምዱን ይመሰርታል፡፡ በተመሰረተው አምድ መነሻ ላይ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ ያስገባል፡፡[4] ዝርዝር ስርዓቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስርዓት 20፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ አ-]+[11ኧ2አ2ኧ3 ]]<br>ቅጣይ  አምድ | ⟶ | [ አ-11ኧ2አ2ኧ3]<br>የአደራረግ ስም |

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች የሚያመለክቱት የአንድን ተግባር አፈፃፀም ማለትም <u>አደራረግን</u> ነው፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሳቢ ዘር በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሳቢ ዘር የሚባሉበት ምክንያት ተናባቢ ድምፃቸውን በመሳሳብ፣ ማለትም በመደጋገም፣ ሰፋ ሰፋ ያለ አምድ ስለሚመሰርቱ ነው፡፡

አስካሁን ከስምና ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ወይም የተለያዩ አናባቢዎችን በግሱ ስር ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ስሞችን እንዴት መመስረት እንደሚቻል አያየን መጥተናል፡፡ በየስርዓቱ የሚፈጠሩ ስሞችን ከትርጉማቸውና ከቅርፃቸው አኳዋያ ለመከፋፈል ሞክረናል፡፡ በዚሁ መሰረት ከግስ ስር የሚመሰረቱትን የአድራጊ፣ የድርጊት፣ የድራጊ፣ የማድረጊያ፣ የአደራረግ፣ የውጤት፣ የሂደት፣ ወዘተ፣ ስም በማለት የአንዱን

---

[4] ባየ (1987) ላይም ይህን ስም የሚመሰርተው ቅጣይ /አስ-/ እንደሆነ ተገልፆ ነበር፡፡ ከዚያ ወዲህ ጉዳዩን እንደገና በመመርመር ቅጣዩ ምናልባት /አስ-/ ሳይሆን፣ /አ-/ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ተችሎአል፡፡ ቅጣዩ /አስ-/ የማይሆንበት ምክንያት ስነ-ድምፃዊ ነው፡፡ /አስ-/ ውስጥ የምትገኘው /ስ/ ከስሩ የመነሻ እግር ጋር ሙሉ በሙሉ ትመሳሰልና ድምፁን ጠብቂ ታስመስለዋለች፡፡ ከላይ በስርዓት (19) የሚታየውም ይኸው ነው፡፡ ችግሩም /ስ/ ከማንኛውም ድምፅ ጋር መመሳሰልዋ ነው፡፡ አንድ ተናባቢ ድምፅ ሊመሳሰል የሚችለው ከማንኛውም ሌላ ተናባቢ ጋር ሳይሆን፣ በቦታ ወይም በአፈጣጠር ባህሪ ከሚቀርበው ሌላ ድምፅ ጋር ነው፡፡ ሁለተኛም /አስ-/ የሚለው ምዕላድ አስደራጊነትን እንጅ አደራረግን የማያመለክት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በንነሳ ምናልባት አደራረግ የሚገለፀው /-11ኧ2አ2ኧ3/ በሚል ዕስር አምድ ነው፤ ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ አምዱ ዕስር ስለሆነ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም ወደ ሙሉ ግስነት ይለወጣል፡፡ /አ-/ በሌሎች ዕስር አምዶች መነሻ ላይ እየገባ ሙሉ ግሶችን የሚመሰርትበት ብዙ ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ /-ገኘ/ ከሚለው ዕስር አምድ መነሻ ላይ በመግባት /አ-ገኘ/ የሚለውን ግስ ይመሰርታል፡፡ ስለዝርዝር ሁኔታው ባየ (1999)ን በተጨማሪ ይመልከቱ፡፡

አይነት ከሌላው መለየት እንደሚቻል አሳይተናል፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የውልድ ቅፅሎችን አመሰራረት እንመረምራለን፡፡

## ውልድ ቅፅሎች

እንደ ስሞች ሁሉ ቅፅሎችም ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ነባር የሚባሉት እንደ ብልህ፣ ትሁት፣ ደግ፣ የዋህ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡ ስለዚህም ነባር ወይም ዘር ይባላሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ አብዛኞቹ ቅፅሎች ውልድ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ የሚወለዱትም ከስሞችና ከግስ ስሮች ወይም እምዶች ላይ ነው፡፡ ያወላለዳቸውን ሁኔታ ከስም ከሚወለዱት በመጀመር ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን፡፡

| <u>ስም</u> | <u>ቅፅል</u> | | |
|---|---|---|---|
| ሀይል | ሀይል-ኧኛኛአ | ሀይለኛ | 1 |
| ቂም | ቂም-ኧኛኛአ | ቂመኛ | |
| ወረት | ወረት-ኧኛኛአ | ወረተኛ | |
| ጉልበት | ጉልበት-ኧኛኛአ | ጉልበተኛ | |
| ጀብድ | ጀብድ-ኧኛኛአ | ጀብደኛ | |

የእነዚህን አይነት ቅፅሎች የአመሰራረት ሂደት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 1፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ስም] + [-ኧኛኛአ]] | ——→ | [ስም-ኧኛኛአ] |
| ቅጣይ | | ቅፅል |

ስርዓቱ አንድ ስም /-ኧኛኛአ/ የሚል ምዕላድ ሲከተለው ቅፅል ይሆናል የሚል ነው፡፡ እንደ *ወረተኛ* ያሉ ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪ ስለሚያመለክቱ፣ የባህሪ ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ ወረተኛ ሰው ነው 2

ብንል፣ <u>ወረተኛ</u> መሆን የካሳ ባህሪ ነው፣ ማለታችን ነው፡፡

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ ከስሞች ላይ /-እም/ ወይም /-እምምአ/ን በመጨመር እንደሚከተለው ይፈጠራሉ፡፡

| ስም | ቅፅል | | |
|---|---|---|---|
| ተራራ | ተራራ-አምምአ | ተራራማ | 3 |
| ድንጋይ | ድንጋይ-አምምአ | ድንጋያማ | |
| አሸዋ | አሸዋ-አምምአ | አሸዋማ | |
| ሆድ | ሆድ-አም | ሆዳም | |
| ወተት | ወተት-አም | ወተታም | |
| ሀብት | ሀብት-አም | ሀብታም | |
| ጥርስ | ጥርስ-አም | ጥርሳም | |
| ጥፍር | ጥፍር-አም | ጥፍራም | |

የእነዚህ አይነት ቅፅሎች የአንድን ነገር በአንድ ቦታ በብዛት መገኘትን ስለሚያመለክቱ፣ የብዛት ወይም የክምችት ቅፅል ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አመሰራረታቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 2፣

| | |
|---|---|
| [[ስም]+[-አም/-አምምአ]] ⟶ | [ቅፅል] |
| ቅጣይ | የብዛት |

የ/-አም/ እና የ/-አምምአ/ አገባብ ስሞቹ በሚጠቁሙት ክምችት ላይ የተመሰረተ ይመስላል፡፡ ነገሩ የሰውነት ክፍል፣ ወይም ከሰውነት ክፍል ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ /-አም/ን የሚያስገባ ይመስላል[5]፡፡ /-አምምአ/ የሚለው ምዕላድ በአብዛኛው ለሰው የማይበጅ ክምችትን የሚያመለክቱ ቅፅሎችን የሚመሰርት ይመስላል፡፡ እንደ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞች ወደ ቅፅልነት የሚለወጡት በዚህ ምዕላድ አማካኝነት ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ እንደ አይናማ፣ ወርቃማ፣ ወዘተ፣ የጥሩ ነገር መግለጫዎች ናቸው፡፡

ሌሎች ቅፅሎች /-አውኢ/ በሚል ምዕላድ አማካኝነት ከስሞች ላይ ይመሰረታሉ፡፡ የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| ስም | ቅፅል | | |
|---|---|---|---|
| ወገን | ወገን-አውኢ | ወገናዊ | 4 |
| ሀገር | ሀገር-አውኢ | ሀገራዊ | |
| ክልል | ክልል-አውኢ | ክልላዊ | |
| ዘመን | ዘመን-አውኢ | ዘመናዊ | |

የእነዚህ አይነት ቅፅሎች ስርዓት እንደሚከተለው ነው፤

[5] ይህ ግን ሁልጊዜ ላይሰራ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ሀብት የሚለው ስም ከሰውነት ክፍል ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ የሚወስደው ግን /-አም/ የሚለውን ምዕላድ ነው፡፡

ስርዓት 3፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ስም] + [-ኣው-ኢ ]] <br> ቅጣይ | ⟶ | [ስም-ኣው-ኢ ] <br> የወገን |

በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ቅፅሎች ወገንን ወይም ክፍልን ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህም በቀደምት ሲቃውንት ዘንድ የወገን ቅፅል በመባል ይታውቃሉ፡፡ በአገባባቸው ከስሞች ጋር ስለሚመሳሰሉ በስም ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) ሰዎቹ ጀግኖች ናቸው 5

ለንል፣ ሰዎቹ የሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ስም ነው፡፡ በእሱ ምትክ ኢትዮጵያዊያን የሚለውን ቃል ብናስገባ፣ አረፍተ ነገሩ፣

(ለ) ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ናቸው

የሚል ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያዊያን የሚለው ቃል ሰዎቹ በሚለው ስም ቦታ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል፡፡ በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያዊያን ያሉ ቃላት እንደ ማንኛውም ስም ቅፅልን እያስቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን፣ እንደ፣

ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን 6

ያሉ ስማዊ ሀረጎችን እናገኛለን፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች እንደ ኢትዮጵያዊ ያሉ ቃላት ስሞች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ባለፈው ክፍል ስለ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ፣ አንድ ቃል በርግጥ ቅፅል ለመባል እንደ፣

ያ በጣም---------- ተማሪ 7

ባለ ሀረግ ውስጥ በሚታየው ክፍት ቦታ ላይ መገኘት መቻል አለበት፣ ብለን ነበር፡፡ በዚህ መስፈርት መሰረት፣ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያለ ቃል በዚህ ቦታ ሊገባ ስለማይችል፣ ቅፅል ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም፣

(ሀ) *ያ በጣም ኢትዮጵያዊ ተማሪ 8

ማለት፣ ተቀባይነት ያለው አባባል አለመሆኑ ነው፡፡ በአንፃሩ ግን፣

(ለ) ያ በጣም መንፈሳዊ ተማሪ

ማሰት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ያለጥርጥር ቅፅል ናቸው፣ ሊባሉ የሚችሉ፣ እንደ መንፈሳዊ፣ ዘመናዊ፣ ፍትህዊ፣ ወቅታዊ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላትም በዚሁ በተራ ቁጥር (3) በትጠቀስው ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ በመሆናቸው፣ ስርዓቱ ቅፅልን ብቻ ሳይሆን ስምንም እንደሚመሰርት መረዳት ይቻላል፡፡ ባጭሩ፣ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ቃላት የወገን ስሞች ሲሆኑ፣ እንደ <u>መንፈሳዊ</u> ያሉት የወገን ቅፅሎች ናቸው፣ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ልዩነታቸውም የቅርፅ ሳይሆን፣ የአገባብ እንደሆነ ከተሰጡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ስሞች፣ በወገን ስምነታቸው ሌሎች ስሞችን እየገለፁ ሲገቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ አገባባቸው ገላጭ ከሆኑት ከቅፅሎች ጋር ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡

ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው 9

ከዚህ በላይ ኢትዮጵያዊያን የሚለው ስም ተማሪዎች የሚለውን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (7) እንደሚታየው፣ <u>በጣም</u> ከሚለው መጣኝ ምዕላድ ጋር ሊገባ አይችልም፡፡ ስለዚህም በተግባሩ ቅፅላዊ፣ በክፍሉ ስማዊ የሆነ ቃል ነው፣

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ከስሞች የሚመሰረቱትን ቅፅሎች ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስማዊ ከሚመስሉ ዕሰር አምዶች ላይ የሚመሰረቱትን እንመለከታለን፡፡

| | <u>አምድ</u> | <u>ቅፅል</u> | 10 |
|---|---|---|---|
| ጥ-ም-ም- | /ጥኧምኣም-/ | /ጥኧምኣም-ኣ/ | ጠማማ |
| ም-ል-ጥ- | /ምኧልኣጥ-/ | /ምኧልኣጥ-ኣ/ | መላጣ |
| ቅ-ር-ፍ-ፍ- | /ቅኧርፍኣፍፍ-/ | /ቅኧርፍኣፍፍ-ኣ/ | ቀርፋፋ |
| ቅ፞-ሽ-ሽ- | /ቅ፞ኧሽኣሽ-/ | /ቅ፞ኧሽኣሽ-ኣ/ | ቆሻሻ |
| ግ-ጥ-ብ- | /ግኧጥኣብ-/ | /ግኧጥኣብ-ኣ/ | ገጣባ |
| ስ-ብ-ር- | /ስኧብኣር-/ | /ስኧብኣር-ኣ/ | ሰባራ |
| ት-ል-ክ-ሽ- | /ትኧልክኣሽሽ- / | /ትኧልክኣሽሽ-ኣ/ | ተልካሻ |

የእነዚህ አይነት ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪያዊ ወይም አካላዊ አይነት በሰሚጠቁሙ፣ የአይነት ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አመሰራረታቸውን እንደሚከተለው አድርጎ ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 4፣

[[ተኧተ(ተ)ኣ-ተ(ተ)-] + [-ኣ] ⟶ [ተኧተ(ተ)ኣተ(ት)-ኣ]]
የአይነት ቅፅል

ከዚህ ላይ /ተኸተ(ተ)እተ(ተ)-/ የሚለው ዕሰር እምድ፣ /ተ-ተ(ተ)-ተ(ተ)/ በሚለው ስር ውስጥ /ኸ/ን እና /እ/ን እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በክፍቶቹ ቦታዎች በማስገባት የተፈጠረ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እምዱ በራሱ ትርጉምም ሆነ የቃል ክፍል የለውም፡፡ ሙሉ ቃል ሆኖ ትርጉምና የቃል ክፍል የሚያገኘው /-እ/ የሚለውን መስራች ምዕላድ ሲያስከትል ነው፡፡ ከዚህም ምዕላድ ገና ትርጉም ያላገ ባዶ ቅርፅ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡

እስካሁን የተመስከትነው ከስሞችና ከስም-መሰል ዕሰር እምዶች ላይ ቅጣዮችን በመጨመር የሚፈጠሩትን ቅፅሎች ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ከግሰ ስር ወይም እምድ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉትን እንመለከታለን፡፡

| ስር | ቅፅል | 11 |
|---|---|---|
| /ሰ-ን-ፍ/ | /ሰኸንኸፍ/ | ሰነፍ |
| /ድ-ን-ዝ/ | /ድኸንኸዝ/ | ደነዝ |
| /ድ-ር-ቅ/ | /ድኸርኸቅ/ | ደረቅ |
| /ው-ድ-ል/ | /ውኸድኸል/ | ወደል |
| /ጥ-ብ-ድ-ል/ | /ጥኸብድኸል/ | ጠብደል |

የእንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች የአመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 5፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ተ-ተ(ተ)-ተ-] | ⟶ | [ተኸተ(ተ)ኸተ]<br>የባህሪ ቅፅል |

ስርዓቱ እንደሚያሳየው፣ ቅፅሎቹ የሚመሰረቱት በየስሮች ውስጥ በሚታዩት ክፍት ቦታዎች /-ኸ-/ የሚለውን እናባቢ በማስገባት ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ባህሪን ወይም መጠንን ስለሚያመለክቱ፣ ቀደም ሲል ካየናቸው፣ እንደ <u>ወረተኛ</u> ካሉ ሌሎች የባህሪ ቅፅሎች ጋር ሊጣቃለሉ ይችሉ ነበር፡፡ የአመሰራረታቸው ስርዓትና የሚመሰረቱበት ክፍል የተለየ በመሆኑ ብቻ ለብቻቸው እንዲታዩ ተደርጓል፡፡ እንደ ዘፈን፣ ወረት፣ ከፈን፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ሰሞችን በዚህ ስርዓት እንደሚፈጠሩ በስም ምስረታ ላይ አይተናል፡፡ ከዚህም ሁለቱ የቃላት ክፍሎች ተመሳሳይ የምስረታ ስርዓት እንደሚከተሉ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ በግስ ስሮች ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ /ኸ/ እና /ኢ/ የሚሉትን እናባቢዎች በማስገባት በሚከተለው ሁኔታ ይመሰረታሉ፡፡

| ስር | ቅፅል | | 12 |
|---|---|---|---|
| /ር-ዝዝ-ም/ | /ርኧዝዝኢም/ | [ርኧዥዥኢም] | ረዥም |
| /ቅ-ጥጥ-ን/ | /ቅኧጥጥኢን/ | [ቅኧጭጭኢን] | ቀጭን |
| /ሀ-ጥጥ-ር/ | /ሀኧጥጥኢር/ | [አጭጭኢር] | አጭር |
| /ጥ-ይይ-ም/ | /ጥኧይይኢም/ | | ጠይም |
| /ፍ-ር - -/ | /ፍኧርኢ-/ | | ፈሪ |

እነዚህም ቀደም ሲል እንዳየናቸው የመጠንና የአይነት ቅፅሎች ናቸው፡፡ እንደ ረዥም ያሉት መጠንን ሲያሳዩ፣ እንደ ቀይ ያሉት ቀለማዊ አይነትን ያመለክታሉ፡፡ በጥቅሉ የአይነት ቅፅል ልንላቸው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡ "ሰውየው ምን አይነት ነው?" ብንባል፤ "ሰውየው አጭር፣ ረዥም፣ ቀይ፣ ወዘተ፡ ነው" ብለን፡ መመለስ እንችላለን፡፡ ርግጥ፡ "ሰውየው ክፉ ነው" ማለትም ይቻላል፡፡ ክፉ የሚለው ቅፅል ግን የሚያመለክተው የሰውየውን አይነት ሳይሆን፡ ግብሩን ነው፡፡ ክፉ የሚያስኘው ክፉ ምግባር ነውና፡፡ ስለዚህም የግብር ቅፅል ልንላቸው እንችላለን፡፡

እንደነዚህ ባሉ ቅፅሎች ውስጥ ቅደመ-መድረሻው ተናባቢ ወደ ላንቃዊነት ይለወጣል፡፡ የለውጡ ምክንያት /-ኢ-/ የምትለዋ አናባቢ ድምፅ ነች፡፡ በስሩ ውስጥ /ዝዝ/ የነበረው ድምፅ በ(ድ)ላንቃዊነቱ ምክንያት ወደ [ዥዥ]፡ እንዲሁም /ጥጥ/ የነበረው ወደ [ጭጭ] ሊለወጥ ችሎአል፡፡ በመጨረሻዎቹ ሁለት ሰሮች ውስጥ የመጨረሻው ተናባቢ ዕግር ተገርዶአል፡፡ እንደዚሁም /ሀ-ጥጥ-ር/ በሚለው ሰር መነሻ ላይ የሚገኘው /ሀ/ ሰለ ተገረደ፡ ቅፅሉ በ/አ/ ሊጀምር ችሎአል፡፡ እነዚህ በስነ-ድምፅ ክፍል ባየነው የግድፈት ስርዓት መሰረት የመጡ ለውጦች ናቸው፡፡

የቅፅሎቹን የአፈጣጠር ስርዓት ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ሰርዓት 6፣

[ ተ-ተ(ተ)-ተ] ⟶ [ ተ-ኧ-ተ(ተ)-ኢ-ተ]
ቅፅል

የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት፡፡

| ሰር | እምድ | ቅፅል | 13 |
|---|---|---|---|
| /ክ-ብ-ር/ | ክ-ብኡር | [ክእብኡር] | ክቡር |
| /ን-ፅ-ሀ/ | ን-ፅኡሀ | [ንእፅኡሀ] | ንፁሀ |
| /ጥ-ቁ-ር/ | ጥ-ቁኡር | [ጥእቅኡር] | ጥቁር |
| /ክ-ፍ - -/ | ክ-ፍኡ | [ክእፍኡ] | ክፉ |
| /ብ-ር-ት- -/ | ብ-ርትኡ | [ብእርትኡ] | ብርቱ |

እንደነዚህ ያሉት፣ አንድ ነገርን ብቻ አያመለክቱም፡፡ ባህሪን፣ አይነትን፣ ግብርን፣ ወዘተ፣ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለት ስሮች፣ የመጨረሻ ተናባቢያቸውን ኅርደዋል፡፡ የቅፅሉቹ ስርዓተ-ፍጥረት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 7፣

| | | |
|---|---|---|
| [ተ-ተ-ተ-(ተ)] | ⟶ | [ተእ-(ተ)ተኡ-(ተ)]<br>ቅፅል |

ስርዓቱ ከመጨረሻው እግር በፊት ባለው ክፍት ቦታ ላይ /-ኡ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ በማስገባት፣ ቅፅሉችን መፍጠር እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሉ የሚታየው /እ/ ስነ-ምፅላዳዊ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተናባቢ ክትትሉሽን ለመስበር የገባ ሰርጎ-ገብ አናባቢ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በየስሮቹ መካከል በሚገኙት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ን እና /-አ-/ን በማስገባትና የቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በማጥበቅ የሚመሰረቱ ሌሎች ቅፅሉች አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| ስር | ቅፅል | 14 |
|---|---|---|
| /ክ-ብብ-ድ/ | /ክኧብብአድ/ | ከባድ |
| /ቅ-ልል-ል/ | /ቅኧልልኣል/ | ቀላል |
| /ድ-ቅቅ-ቅ/ | /ድኧቅቅኣቅ/ | ደቃቅ |
| /ድ-ምም-ቅ/ | /ድኧምምአቅ/ | ደማቅ |
| /ው-ልል-ድ/ | /ውኧልልአድ/ | ወላድ |
| /ድ-ፍፍ-ር/ | /ድኧፍፍአር/ | ደፋር |

እንደነዚህ ያሉት ይዘትን ወይም ሁኔታን ስለሚያመለክቱ የይዘት ቅፅሉች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አፈጣጠራቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 8፣

| | | |
|---|---|---|
| [ተ-ተ-ተ-] | ⟶ | [ተኧተተአተ]<br>የይዘት ቅፅል |

እስካሁን ያየናቸው ልዩ ልዩ ስርዓቶች በቋዋንቋዋው ውስጥ በጥቅም ላይ የሚገኙትን ስሞችና ቅፅሉች ውስጣዊ አቀነጃጀት እንድንመረምር ብቻ ሳይሆን፣ በጥቅም ላይ ያልዋሉ አዳዲስ ቃላትንም እንድንፈጥርና ለተለያዩ አዳዲስ ፅንሰ-

ሀሳብ ወይም ክስተት ስያሜ በማድረግ አንድንጠቀምባቸው የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስርዓቶቹ የተወሰኑ ቢሆኑም ሊፈጥሩት የሚችሉት የቃላት መጠን ወሰን የለውም፡፡ ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት እንደ ዘላል፣ ደባቅ፣ ቀዳድ፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ቅፅሎችን መፍጠርና ለአዳዲስ ቅፅላዊ ፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ በየቦታው እየዞረ የሀሰት ወሬ የሚነዛን ሰው ቀዳድ ልንለው እንችላለን፡፡ ወሬ የሚቀድ ማለት ነው፡፡ ወደሚቀጥለው ክፍል እንሂድ፡፡

## ውልድ ግሶች

ባለፉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች ውስጥ ስሞች ከቅፅሎችና ከግስ ስሮች፣ ቅፅሎችም ከስሞችና ከስሮች እንዴት እንደሚመሰረቱ አይተናል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ፣ የቃላቱ የአመሰራረት ስርዓቶች አንድን የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለውጡ ናቸው፡፡ ስምን ወደ ቅፅል፣ ቅፅልን ወደ ስም፣ እንዲሁም ግስን ወደ ስም ወይም ወደ ቅፅል የሚለውጡ ስለሆኑ፣ ክፍል ለዋጭ ስርዓቶች ልንላቸው እንችላለን፡፡ በዚህም ምክንያት ክፍል ከማይለውጡት የርባታ ስርዓቶች ይለያሉ፡፡

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ግሶች እንዴት እንደሚመሰረቱ እንመለከታለን፡፡ የግሶች የአመሰራረት ስርዓት ከስሞችና ከቅፅሎች የአመሰራረት ስርዓት የተለየ ነው፡፡ ስሞችና ቅፅሎች ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ሲመሰረቱ፣ ግሶች ግን ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ ሳይሆን፣ በአብዛኛው ከስር ላይ በአናባቢዎች አማካኝነት ከሚመሰረቱ አሀዶች ላይ ነው፡፡ አሀዶቹ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አዕማድ በመባል ይታወቃሉ፡፡ አዕማድ ቀደም ሲል አምድ እያልን ስንጠራው የነበረው ቃል የብዙ ቁጥር ነው፡፡ በሊቃውንቱ አመለካከት፣ ከየስሩ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉት የአዕማድ አይነቶች ሰባት ናቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አደራጊ | ተደራጊ | 1 |
| አስደራጊ | | |
| አዳራጊ | ተዳራጊ | |
| አደራራጊ | ተደራራጊ | |

በእኔ እምነት የአዕማዱ አይነት በነዚህ ብቻ የሚወሰን አይመስለኝም፡፡ ያልተጠቀሱ አዕማድ ያሉ ይመስለኛል፡፡ ከነዚህም አንዱ የአንድን ድርጊት መደጋገም ወይም መዘውተር የሚያመለክተው ዕሰር አምድ ነው፡፡ ደጋጋሚ ወይም ደራራጊ አምድ ልንለው እንችላለን፡፡ ሌላው ድርጊትን የሚያመለክት ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ መዳረግን የሚያሳይ ነው፡፡ ዳራጊ አምድ ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የአዕማዱ ዝርዝር የሚከተለው መሆን አለበት፡፡

2

ደራጊ
አድራጊ
አስደራጊ
→ ተደራጊ

ዳራጊ
አዳራጊ (ሀ)
አዳራጊ (ለ)
→ ተዳራጊ

ደራራጊ
አደራራጊ (ሀ)
አደራራጊ (ለ)
→ ተደራራጊ

ከዝርዝሩ እንደሚታየው 12 የአዕማድ አይነቶች አሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሰን የእያንዳንዳቸውን ዝርዝር የአመሰራረት ሁኔታ እንመልከታለን፡፡

## ደራጊ አዕማድ

ደራጊ አዕማድ የሚባሉት ያለምንም መሰራች ቅጣይ ምዕላድ በቀጥታ በየግሱ ስር ውስጥ /-ኧ-/ የሚለውን እናባቢ በማስገባት የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ የሚገባው እናባቢ ቁጥር እንደ አዕማዱ አይነትና እንደ ተናባቢው ቁጥር ይለያያል፡፡ ለባለ ሶስት እግር ቀዳማይ አንቀፅ የሚያስፈልገው እናባቢ ሁለት ሲሆን፣ ለባለ አራት እግር የሚያስፈልገው ሶስት ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

1

| ስር | ቀዳማይ አዕማድ | |
|---|---|---|
| /ስ-ብ-ር/ | /ስኧብብኧር-/ | ሰበር- |
| /ል-ም-ን/ | /ልኧምምኧን-/ | ለመን- |
| /ፍ-ል-ግ/ | /ፍኧልልኧግ-/ | ፈለግ- |
| /ድ-ም-ር/ | /ድኧምምኧር-/ | ደመር- |
| /ጅ-ም-ር/ | /ጅኧምምኧር-/ | ጀመር- |
| /ድ-ግ-ስ/ | /ድኧግግኧስ-/ | ደገስ- |

እንደነዚህ ያሉ ዕስር የቀዳማይ አንቀፅ አዕማድ ናቸው፡፡ ነፃ የሚሆኑት መደብ አመልካች ቅጣዮችን ሲያስከትሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰበር- የሚለው እምድ አንደኛ መደብ አመልካች የሆነውን /-ከኡ/ን ሲያስከትል፣ ሰበር-ኩ ይሆናል፡፡ ይህም ዕስር ሳይሆን፣ ነፃ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፡ የእነዚህ አይነት ግሶች ያለቀ ድርጊትን ስለሚገልፁ፡ ደራጊ አዕማድ ብለናቸዋል፡፡ ድርጊቱ ያለቀ መሆኑን የሚገልፁት በሰሩ መካከል በሚገባው እናባቢና በቅድመ-

መድረሻው ተናባቢ ድምፅ ጥብቀት ነው፡፡ ስርዓተ-ፍጥረታቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 1፣

| ስር | | ደራጊ አምድ |
|---|---|---|
| [1 - 22 - 3] | ⟶ | [1ኧ22ኧ3-] |
| /ድ - ግግ - ስ-/ | | [ድኧግግኧስ-] |

በመጀመሪያው ቅንፍ ውስጥ የሚታዩት ቁጥሮች የሰሩን ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ፡፡ ስሩ ከሶስት የተለያዩ ተናባቢዎች እንደተመሰረተ ያመለክታሉ፡፡ አምዱ ከመነሻውና ከቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በመጨመርና ቅድመ-መድረሻውን ተናባቢ በማጥበቅ ይመሰረታል፡፡ ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ጥብቅ መሆኑን ለማመልከት ቁጥሩን ደግመን እንፅፈዋለን፡፡

ደራጊ ግሶች ድርጊትን ሰለሚያመለክቱ በጥቅሉ ገቢር ግሶች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ እንደ መዋቅራዊ ባህሪያቸውም _ሳቢ_ ወይም _ኢሳቢ_ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ሳቢ የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ጋር የሚዋቀሩት ሲሆኑ፣ ኢሳቢ የሚባሉት ይህን ማድረግ የማይችሉት ናቸው፡፡ ዝርዝር ልዩነታቸውን በክፍል ሶስት እንመለከተዋለን፤ ለአብነት ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) አስቴር [ልብስ ተኮሰች] 2
(ለ) እስቴር [---- ሳቀች]

በመጀመሪያው ምሳሌ _ተኮሰች_ የሚለው ግስ _ልብስ_ ከሚለው መሙሊያ ስም ጋር ተዋቅሮአል፡፡ ስሙ የግሱ ተሳቢ፣ ማለትም ተጎታች ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ግን _ሳቀች_ የሚለው ግስ ያለምንም ተሳቢ ብቻውን ይታያል፡፡ ሁለቱም ግሶች ገቢር ይሁኑ እንጅ፣ የመጀመሪያው ብቻ ሳቢ ነው፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ተሻጋሪ ግስ በመባል ይታወቃል፡፡ ድርጊቱን ወደ ተሳቢው ስም የማሻገር ባህሪ አለው፡፡

## አድራጊ አዕማድ

አድራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ሰው አንድን ድርጊት እሱ ራሱ በሌላ ነገር ላይ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አመሰራረታቸው ከደራጊ አዕማድ ላይ /አ-/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው፡፡ የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡